Fesseha Atlaw
Collection

ወፌ ቆመች

ከወንድዬ አሊ

ማውጫ

መግቢያ .... ፪
በስንኝ ሲሰክሩ.. 1
በመሰንቆ.. 3
እኮ ! 4
ዝም ያሰረው ፍቅር 5
አውላላው ላይ.. 6
የእንባ ሥርዓቱ.. 7
የእኔና-እኔ ነገር.. 8
ውጋት 10
ድሮ 12
አሹ ! 13
እዚህ ላይ ነው ቁምነገሩ 13
ሽው-እልም.. 18
ፉጨት.. 19
አስቸግርህ ባጣ.. 20
ኮከቡን.. 22
ብቻውን...!.. 23
ከተከርቸም 24
ትዝታ 25
ሽምቀቆ 26

መ ግ ቢ ያ

"ሥነ ግጥም ከሕይወት ወስዶን ፣ ከተፈጥሮ ምስጢር አጣል
ን መልሰን ለሕይወት የምናቀርባት ገጸ በረከት ናት፡-መስተዋት።
ሳችም ወፈረች፣ነጣችም ወዛች - ሕይወት መልኳን፣መልከ ባሕሪ
ን ታይበታለች ።

"የውበት መግለጫ መደምደሚያ ናት " ለሚሉትም የኪነ
ጥበቡ ሰዎች የብሂላቸው ተመሳጭ ነኝ ።

የገጣሚውስ ነገር - ? እሱማ ! የሥነ ውበት ፣ የሕይወት ባለ
አደራ ነው ። ባለማተብ ባለ አደራ ። የዚያች ጥበብ ከራማ "በል"
ያለውን ነፍስያው ላይ የተሸመነውን መጣፊያ ሳይደረትበት ያለ
እንከን ያስተላለፈ፣ ያቀበለ ጊዜ ማተቡን ለዘለዓለማዊነት የሚያጸና።

ባለ አደራው አሣረኛ ነው ። ውበትን የሚፈልገው አበባ ላይ
ብቻ አይደለም ፣ባጠራትም እሾህ ላይም እንጂ ። " ውበት -የመል
ካሞች መግለጫ (መወኪያ) ብቻ ሳትሆን - የማንኛውም ነገር ጥሩ
ምስል (ትርጉም) ናት " እንዲል ኢማኑኤል ካንት ።

የሥነ ግጥምና የገጣሚው (የዛሩና የፈረሰኛውን) አኳኋን
አንዳንዴ በዐይነ ሕሊናዬ ሲደምቅ ፡- ሥነ ግጥምን የስግደት ያህል
ክብር እንደምሰጠው ለመግለጥ ስል ነው የላይኛውን ሁሉ ያተት
ኩት ።

በመገረሞቹ መካከልም ፡- በሬውን ወይ ገበሬውን መሆኑ ሳይ ለይልኝ በየአጋጣሚው ከጫርኳቸው በርካታ ግጥሞች መካከል ነው፣ በዚች ጥራዝ ከፊሎቹ ተሰባስበው ለሕትመት የበቁት ። የቀረውን ሁሉ እነሱ ሊነግሩልኝ ይገባቸዋል መሰል ።

ለተለየ አገላለጽ - በተለየ አግባብ የተጠቀምኩባቸውን ፣ እንዲሁም ቀበሌኛ ለመሰሉኝ ቃላትና ሐረጎች መፍቻና ማብራሪያ ተዘጋጅቶላቸዋል ።

ወንድዬ አሊ

መስከረም 1984

በስንኝ ሲሰክሩ

የገደል ፏፏቴ ፣
የገደል ፏፏቴ ፣

መልከም አፈሳሰስ ፣ . . .ወድቆ ማይሰበር ፣
ፈሶ ማይደፋ ፣ . . . . . . .ጮኾ ማያሸብር ፤

የገደል ማሚቶ ፣
የገደል ማሚቶ ፣

ልቦና ጫፍ ፈልቆ . . . ልቦና ጫፍ ወጥቶ
ከዳሩ ተጋጭቶ . . . ከዚያው ዳር ተላግቶ ፣
ግም ! ዷ . . .!
ግም ! ዷ . . .!
ድንቅዬ - ወለሏታ ፣
የጭብጦች - ቱማታ ፤

የገደል ጨረባ ፣
የገደል ጨረባ ፣

ከፍ ዝቁን ረግቦ ፣
ወደ ሰርጡ ሰርጦ . . .ከሰርጡ ቀንጭቦ ፣
ሰርጡን ተቀናጭቦ፣

ወደ አፋፉ ጉኖ ፣
ቋጥኝ ላይ አንኩቶ . . . ከበድኑ ተባድኖ ፣
ቋጥኝ ላይ በቁጢጥ ፣
ሲያልሙ ወደ ሰርጥ ፤

የወንዝ ዳር ንዳድ ፣
በቄጤማ ሰደድ ፣

ቢነድም እርጥቡ . . . ቢቃጠል ከእናቱ ፣
ቢገፋም ወንዙ አለ . . . ገፍቶስ የት አባቱ ?
አለቦታው ነዶ . . . . . ሰደድ ባመልግም ፣
ከእናቱ ሲቃጠል . . . . ሥሩን አለምልሞ ፤

የዳገት ሩጫ ፣
በሕልም ሽምጥጫ ፣

ከናዳ ግልምጫ ፣ . . . ሸሽቶ ለማምለጫ ፣
ትንፋሽን በዋንጫ . . . መሳብ በቡጥጫ ፣
መሮጥ በቡጥጫ . . . ከአቀበት ፍጥጫ ፤

ገደል ጫፍ ላይ በቅሎ ፣
ዋርካው ጥላ ጥሎ ፣
እሱ ከተገኘ ፣
ምኝነት ተሞኘ ።

. . . በዋርካው ጥላ ሥር ፣
ተቀዛቅዞ በአየር ፣
በዋርካው ጥላ ሥር ፣ . . . ግራ ቀኝ አማትሮ ፣
ውበትን በርብሮ ፣ . . . ውበትን ቀምሮ ፣
አዳር ከተገኘ ፣
ምኝነት ተሞኘ ።

እንዲህ ነው ምስጢሩ ፣
በስንኝ ሲሰክሩ ።
ከጐን ወደ ግድም . . . አግድሙን ተልጎ
ከአናት ወደ ግርጌ . . . ሽርተቴ ተንዶ ፣

. . . . አግድም መሰበቁ ፣
. . . . ቁልቁል መደቅደቁ ፣

ከዚህ ጐን - እዚያ ጐን . . . ድረሱን መሰበቅ ፣
ውስጠ - ውጭ - ፍልቂቃ . . . ከሩሕ መተናነቅ ፤
እንዲህ ነው ምስጢሩ ፣
በስንኝ ሲሰክሩ ።

ለዘሬረወርቅ ለውለሉም

16-9-82

በመሰንቆ

ባለጭራው - ይኸ ጫሪ ፣
ልሳነ ነፍስ - አናጋሪ ፣
ጭራውን - በገዘገዘ ፣
የእምና ካቡ - ረዘረዘ፤
ከርሞም - መካረሚያ አጣ ፣
በጭራው መስህብ - ግዱን መጣ ፤

ዋ ! ትበል አሞራ ፣
ለዚህ ባለጭራ ።

ባለጭራው - ይኸ ጫሪ ፣
ልሳነ ነፍስ - አናጋሪ ፣
ጭራውን - በጫረው ፣ . . .

. . . ትናንትናዬን - አመሰው ፤
አሁኔን - አለሳለሰው ፣
ነገዬን - ቀድሞ ጨበጠው ።

ዋ ! ዋ ! ትበል አሞራ ፣
ለዚህ ባለጭራ ፣
ሽሽግዬን - በገለጠ ፣
የድብቄን - በቢጠጠ ።

13-11-82

እኮ

. . .እኮ ! እሱን አይደለ የምልህ !!
ሲሳብ . . .ሲሳሳብ . . . እንተንትህ ፣
የናፈቀውን ፣- እየጠራ . . . እየጠራ ፣
የራሱን ክፋና ደግ ፡- እያጣራ . . . እያጣራ ፣
እንደገናም እየተሳበ . . . እየተሳበ ፣
በምክንያትህ ምክንያት . . . እየሳበ እየሳበ ፣
የጨበጠውን ሲያጠብቅ . . . እፍኙ ባለመሙላቱ ፣
ለሌላ ሩቅ ሲዘረጋ . . . ቅርብን ከመጫማቱ . . .
ግና ይበልጡን ፡- የፍጻሜህ ጣራ ርቃ ፣
ተዛንፋ ፡- የጉጉትህ ሚዛን ሳንቃ ፣
ብርቱ ምኞትህ ፡--" አፉ ዋሻ" ፣
ቢከትም - የዕድል ፈንታን ስዕለት ጉርሻ ፣
እንዳግበሰበሰ - ከቶ አላምጦ ፣
ባምሮትህ - የምራቅ ጐርፍ ነድቶ ውጦ ፣
አዲስ አጨቀበት እንጂ . . . ጠገብኩን አለማለሙ ፣
መሳሳብህ - አለማቆሙ . . .
እሱን አይደል - ! የምልህ . . . የመሻትህ ሰበብ ሰበቡ ፣
ሕግስ ደንብስ - ዐዋጅ የሌለበቱ ፣
እኮ ! . . .እሱን አይደል የምልህ !
በመሻትህ ጉልበት መታሸቱን ዘላለምህ ።

13-6-81

ዝም ያሰረው ፍቅር

ለአጋጣሚ ብካይ ፡- ውሳኔ ውስን ፣
ስናደባ ፡- በማን ያውቃል ? - ሰበብ ተገን ፣
ጊዜ - ለጊዜ ፡- አገዘ ፣
የዕድሜን ድሪቶ ፡- አጋዘ ።
እኛም ፡- በጊዜ ጊዜ ፣
ጊዜም ፡- በኛ ጉዳይ አባዜ ፣
እንዳንሞሻሸር - ተላለፍን ፣
ስናደባ - በማን ያውቃል ?- ሰበብ ተገን ።

አይዘመሙ ዘሞ ዝምታ ፣
የልሳናችን ወለምታ ።

የትኩሳታችን እንፋሎት . . . ሊወጣ ቀን ሲዳዳ ፣
የልባችን ዝግ ገሞራ . . . እባጩ እንዳይፈነዳ ፣
በማይም ረቂቅነታችን . . . . . . ተጽናንቶ ፣
የማናውቀውን ጨለማ . . . . . . ፈርቶ ፣
ከትናጋችን ተዳርቶ ተመለሰ ፣
ያኔ . . . ጊዜ በኛ ላይ ነገሠ ። . . .

. . . አይዘመሙ ዘሞ ዝምታ
የልሳናችን ወለምታ ።

አዕምሮአችን ነግሮን እያለ ፣
እኛነታችንን ጠፍንገን ፡- ምክንያታችን ማለለ ።

- ታዲያ በመሐል ጣልቃ ገብቶ
ነጋሪት አስጐስሞ - መለከት አስነፍቶ ፣
ደቂቃ ሰዓት ፣ ቀንና ወራት አጃቦቹን ፣
አስደልቆብን ፡-አናፍተውበት በናላችን ፣

ዕድሜ ከጊዜ መክሮብን ፣
ጊዜ በኛ ላይ ነገሠብን ።

አይዘሙ ዘሞ ዝምታ ፣
የልሳናችን ወለምታ ፣
መውደድ በውስጣችን መክነ ፣
ፍቅር በውስጣችን በደነ ።
እረፋው ።

2-9-80

አውላላው ላይ

አውላላው - ላይ . . .

የድል ፋና ያየህበት . . . . . የደመናት ቀዳዳ ፣
የተስፋህ ጉም ሳይዘንብ . . . ቢሰወር ከሰማያት ሰሌዳ ፣
የሾላህ ፍሬ ባይበስል . . . ልክ ጓዳህ እንደሳሳ ፣
እምልጦህ-ከባሕሩ ቢወድቅ . . . ያጠመድከው የወርቅ ዓሣ ፣

አውላላው ላይ . . .

አዘምር ብለህ - አዝመራ ፣
ዕዳሪ ቆፍረህ - ብትዘራ ፣
ቡቃያው - እንዳማረ ፣
"ቡቃያ ብቻ" - ሆኖ ቀረ
ቢሉህ
ምን - ትላለህ - ?

አውላላው - ላይ . . .

እንዲህ . . . . ከወንዙ ማዶ ፣
ግብህ . . . . በተስፋ ጀልባ ነጉዶ ፣
ከመዳረሻህ . . . ከግብህ በር ፣

እንተና አንተ . . .ስትቀር ፣
በውስጥህ የማዕበል ግርሻ . . .

የድርጊት ጀልባህ ቢሰበር ፣

ምን ትላለህ ?
ከማንስ ትጣላለህ ?
እንደሰው ሰውነትህ ፣
ምን ትላለህ ?
ውነት ምን ትላለህ ?
በናትህ ።

የካቲት 1980

የእንባ ሥርዓቱ

የሰው - ሰውነቱ ፣
መታሰሪያ - እትብቱ ፣
እጥንት - ከጅማቱ ፣
የደም ደም - ስበቱ ፣
የወል ውል - ማምጣቱ ።

እንዲያው መገናኘት . . . . . በጨዋታ ለዛ ፣
ከምድጃ ዳር ወሬ . . . . . መደብ ላይ እጐዛ ፣
አዎ!አንድ መደብ መዋል . . . . . . በወግ ወግ ገበታ ፣
የሶታነት ቀልዱ . . . . . በኋላም ከመሸ የሽበት ትዝታ
በጢት በማሲዳ . . . . . ማታም - ማታ ማታ ፣

ውል . . . . .ሲል !
ሸው . . . . .ሲል ! . . .መቅረቱ
ተረት ሆኖ ርስቱ ፡-
ያኔ ይጀምራል - የእንባ ሥርዓቱ ።

በእንዲያ, ዲያም - ከመጣ . . . . . . ልለፍ ካሉ አቅርሮ ፣
ግድቡን ከሞላ . . . . በገታው አምርሮ ፣

እንባን አትከልክሉት ! . . . ይውረድ በዩን ጥሶ ፣
አቦ ! እንባን አትገድቡት . . . ይፍሰስ ቆቡን ድሶ ፣
ቁርሾን ከልብ ውስጥ . . . ማዲያት ከገጽታ ፣
እስቲ ይጠብ ተውት . . . ሞታቸውን ይፍታ ።

15-3-78

የእኔና - እኔ ነገር

እኔና - ብቻዬ ፣
ትንኟ - ታዛዬ ፣
ኮከብ . . . ታዛቢያችን ፣
ብሉን - ቁጭ እልን ።

እኔና እኔ - እንዲ ቀረን ፣
ለብቻችን ፣
ወደ ኋላም . . . ወደፊትም . . . ጊዜን አሰላነው ፣
ዘመን :- ከፋም . . . ደግም . . . አለው ፣

" . . .የዘመን ምርኩዙ . . . የሰው ሰውነቱ ፣
ለራስህ ብትከፋ . . . ጨለማህ ብርታቱ ፣"

ብትለኝ ብቻዬ :-

"እንግዲያማ ደጋ . . . . . ከፋቱን እስታውቀው ፣
በሬን (የተስፋዬን) . . . . . አልከፍተው - አልዘጋው ፣
ሁሉን ላንቺ ትቸው . . . . አፊን በእጄ ልምታ ፣"
አልኳታ ።

ይኸን ሰሞንስ የብቻ ፣
የኔ በኔ ዘመቻ ።
የኔና - እኔ ነገር ፣
ሁሌ - በክርክር ፣
እንዳለን :-
አለን ።

- አንድ ቀን . . . ዘንግቼ ኖሮ ፣
የሆነ አዚም . . . ጠልፎ አሳብሮ ፣
ዘረጠጠኝና - ጣለኝ ፣
መጋደሚያውም - ለሰለሰኝ ፣

ለወዲያው :- ምንተዳዬም አላልኩ ፣
ኋላ . . . ቀስ - በቀስ ለመድኩ ፣
ወይ ሕመሜ ፣
እኔን እስረስቶኝ ከርሜ ፣
በገዛ እጄ ፣
ኑሮ ብዬ ለምጄ ፤

የኔው ሕመም ሳቢያ ሆኖ . . . ገባን ሸንጎ
እናንጓለው ተባብለን . . . ሥራ'ዩን ምራጭ ከበጎ ፤
እና እኔና እኔም ስንወያይ ፣

— አልጋዬ ላይ ፣

ቅናት የለው ገላጋይ ፣
በዳይ የለ - ተበዳይ ፣
ማን ያሸንፍ ?
ማን ይሸነፍ ?

በጥል ተርታ ያዩትማ . . . ጥሉ ፣
ኩበት ሥጋን ጠበሰው . . . አሉ ፤
አሉ ።

እኔና እኔም . . . ባዳነታችን ፤
እያደር - ተገለጠልን ።

28-5-80

" ውጋት "

ጣቶቼ - ጥቅሻ ላይ ፤
ሕሊናዬም - የወግ ብካይ ፤
ብራናውም - ገና ለዛዛ ፤
ቀለሙም - ገና ፈዛዛ ፤
መሆኑን ነግሬሽ ምነው !?
ውቃቢሽ የማይለመነው ።

ምነው ? .... ውልደትሽ የጥንት አይደለም እንደ
ድባብ ጠል .... ባልቀባው ዘዴ ፤
በሞኝ ፍቅር ... የገለብሽኝ ፤
አደባባይ ... ያሳቀልሽኝ ፤
... የበተንሽኝ ፤
... የረጩሽኝ ፤

ለጠፍ ጨረቃ ... የገለጥሽኝ ፤
... የዘራሽኝ ፤

ምነው ! ?

የአድባር ምሷን - ለመቋረሱ ፤
በአልጋ - ለመቆራቆሱ ፤
ጉባጣችንን - ለማረቁ ፤
ጥላችንን - ለማስታረቁ፤
ወይም - ለመነዳደፉ ፤
ለሞላ ጉደል - ትርፉ ፤
ምነው ፡ - እንዲህ መጣደፉ ?

እባክሽማ ...! ተይኝ ፤
ፍቅርሽን ተለመኝኝ ፤

ቅዠትሽን - እንደ ሕልሜ ፤
እምነትሽን - እንደ ስሜ ፤
ያየሽውን - እኔ ማየው ፤
ዘላለምሽን - እኔ ማምነው ፤
የማልረሳው ፤
የምጠራው ፤ . . .

ቋጠሮቻችንን - ጉዝጉዘን ፤
ዕጣን ከርቤ - አጫጭሰን ፤
በሉባንጃ - ታጥነን ሙቀን ፤
ሽቶአችንን - አርከፍክፈን ፤
በአምባር - ውበት - ደምቀን ለብሰን ፤
በአቦል ጀባ - ተመራርቀን ፤
በጸጥታ ፋና - መቅረዝ ፤
ረ . . . ጋ . . . ! ብለን - ስንቀዝዝ ፤
ያኔዬ ነው ፡-
ውቃቢሽን - የምደፍረው ፤
ዛውያሽን - የምገልጠው ፤
የአድባር ምሱን - የምሰጠው ፤
አዎ - ያኔ ይሁንልኝማ ፤
የምንጋፈፍበት ሸማ ።

እባክሽማ ! ተይኝ ፤
በሰደድሽ - አትግረፊኝ ፤
ሕይወት ፤
ውበት ፤
"እንከን - ጉድፍ . . . ድርብ ዋሾ ፤ "
ነው እንዳንል . . . " የአበቅ እርሾ ፤ "

ምረጭልኝ እንጂ - ቦታ ፤
ቅጠሪኝ እንጂ - ለቆይታ ።

ያኔዬ . . .ጣቶቼም - ጥቅሻ አያበዙ ፤
ይልቅ እንጂ ብዕር ቢመዙ ፤
ቀለሚም ነትሮ ተሰብቆ ፤
ውን - ይስላል - ከእውን ታርቆ ።

ያኔዬ . . .

ሐቃችንም - አይሻክርም ፤
ፍቅራችንም - ሸማ አይቀድም ። . . .
“ሕይወት ፤
ውበት
እንከን - ጉድፍ . . . የአበቅ እርሾ ፤”
ብቻ - አንልም . . . . . “ ድርብ ዋሾ ።”
እባክሽማ ! ተይኝ ፤
ፍቅርሽን ተለመኝኝ ።

7-5-82

ድ ሮ

ድሮ . . .ልክ አለው እንዴ - ጉበዝ ?
“መቼ -? ”አለው እንዴ ድሮ ?
“ነበርን ” በነበር ስሌት አስሮ ፤
ታዝሎ በነበር አንቀልባ ፤
ሳይኖር - ኑሮን ቢያባባ . . .
ድሮ . . . ልክ አለው እንዴ ጉበዝ ?
ድሮ . . . ልክ አለው እንዴ ጉበዝ ?
“ስንት -?” አለው እንዴ ድሮ
እልፊትን በባዶ ትውስታ አስሮ
ነገን በማይወልድ ትዝታ
ውሎ ቢያውለን ተረብ ተርታ ፤
“ ይህን ጊዜ ” . . . . የሚሉቱ ፤
“ ከይህ ወዲህ ” . . . የሚሉቱ ፤
ምንድን ነው ድሮ መስፈርቱ ?
ድሮ ልክ አለው እንዴ ጉበዝ ?

11-11-89

“ እሹ ! ”

በስሌት ናላ - መጨኔቁ ፤
በትንቢቱ - መታመቁ ፤
በምሮታችን - መንከልከሉ ፤
በአዚማችን - መነሁለሉ ፤ . . . . .

በተስፋ - ስንንጠለጠል . . .
በጉጉት - ስንቀጣጠል . . . .

ልብ ማፈኑ ነው ፤ . . . መጠበቡ . . . ሕይወት ውበቱ
‘እሰይ ! ! ” -ተሰወረብን - “ ነግ ምን ይሆን . . .?” ክስተቱ ።

13-4-82

እዚህ ላይ ነው ቁም ነገሩ

ኚኛው . . . ገና በጫካ ፡- ቅጠል ፍራፍሬ በጥሶ ፤
ለአዳሩ - ሥራሥር ምሶ ፤

ንኛው . . . ገና በዋሻ - የመኖር ዳዴ ሲጀምር ፤
ቀለቡን - አውሬ ሲያባርር ፤
ፍልቅልቅ - እመቤት አገር ፤
ግዮን ምንጮች ላይ ተንፈራጣ ፤
ዳሸንን - ደፍታ - ባርኔጣ ፤
ቀይ ባሕር - ግምጃ ጥልቷ ፤
አዋሽም - ለመቀነቷ ፤

ሚዳ . . . ዱር ጫካው ጥብጣቡ፣
የለምለም - ቀሚሷ ክበቡ ፤

ከአራት ማ'ዘን - ያለ አምሳያ ፤
እመቤት አለች - ውብ - ቡቃያ ።

የአንዱ ዘር . . . ገና በጫካ - ቅጠል ፍራፍሬ በጥሶ ፤
ለአዳሩ - ሥራ ሥር ምሶ ፤

ሌላውም . . . ገና በዋሻ - የመኖር ዳዴ ሲጀምር ፤
- ቀለቡን አውሬ ሲያባርር ፤

ይቺ ሽሙንሙን - የውበት ምድር ፤
በራሷ ፊደል - ፊድላ . . . ከኪነ ጥበብ - ጥበብ ዘርታ
ቅኔ መወድስ - ያበሠረች . . . አክሱም ላሊበላን አምርታ
የጥቁር ዓለም - መናገሻ ፤
ብትኖር አንዲት አበሻ . . .

ከጥበቦቿ - ጥበብ - ዘርፈው ፤
ከፊደሎቿ - ልሳን ሰርቀው ፤
በጥበቧ - ዐይን ሲከፍቱ ፤
በቋንቋዋም - አፍ ሲፈቱ ፤
ያኔ - የጀመረ ነው ፅንሱ ፤
ውብ - አካሏን የመቁረሱ ፤
ጥበብ ብልጭታዋን - የማክሰሉ ፤
ታሪክ ሙዳይዋን - መዘንጠሉ ፤
የሩቅ ጅምር ነው ሥሩ ፤
መቅረዟን - የመሰወሩ ።

. . . ሥልጣኔዋን በአፍ ብልጫ ፤-ዘሩን ከአቁማዳው መደበቁ
በቅናት መዶለታቸው ፤ ቅድመ ታሪኳን ሊናጠቁ ፤

ዋል - አደር ያለ ነው ፅንሱ ፤
ነገድ ከነገድ - ማናከሱ ።

ታዲያ እኮ ! . . . ፅንስ ይወርዳል ፤
ወይ ይወለዳል ፤

እንደዚሁ እንኳን ፡-

በአንድ ወቅት - የታሪክ ጉዞ ፤
አቅኚነት - በዕብደት ተይዞ ፤
ጥንብ ያየ - ጆቢራ ነገር ፤
ሲራኮት - ነጫጭ የሰው ዘር ፤ . . .በጥቁር የአፍሪካ ምድር ፤
ሲመትር ፡ ሲቀይስ - መሬት በስንዝር ፤
ምስጋን ለወላድ እንጂ . . .ይቺ ግን የአበሻ ምድር ፤
ቢመኙም - አልነኳት ነበር ።

ሽሉ ግን ቆዩ . . . . የነሮሙቹ ፤
በሰው ንብረት . . . . የጌቶቹ ፤
በሰው ጥበብ . . . . ፈላስሞቹ ፤
የሰው አገር . . . . አቅኚዎቹ ።

ግና ሽል . . . ይወለዳል ፤
- ወይ ይወርዳል ።

ትንቧለልን - ውብ ቡቃያ . . .ውብ አካሏን ለመቁረሱ፤
መዳራቱ - መጣቀሱ ፤

በአድማ ሴራ ርብርብ . . . ሲያጮልቁ በየጎጡ ፤
ሲፈትሹ . . . ሲዳፈሩ በየቆጡ ፤
ያልሞከሩት ምን ነበረ ? . . . በዶጋሊ በመቱማ ፤
ኢትዮጵያዬ ጀግና ወልዳ . . . ጀግና ገሎ ባይሞትማ ። . . .

ምስጋን ! . . . ለወላድ መሬት ለአድባሩ ፤
ጀግና ሞልቷል - በየበሩ ፤
በርግጥ - ብዙ ጀግኖች ነበሩ ።

እዚህ ላይ ነው ጐበዝ !

እዚህ ላይ ነው ቁም ነገሩ ፤
የፊልሚያው ሁሉ መነሻ . . .ዓይነትያነት ሥሩ ፤
የነዶጋሊ ገድለ - ታምሩ ።

በዜግነት - ቤዛ ክብሩ ፤
አንድነት - አገር ማክበሩ ፤
ጥቁር "ሰው" - መሆኑን ማስመስከሩ ፤

የአበሻ ኬላ - መታፈሩ ፣
በጠላት ምላስ - መነገሩ ።

ምስጋን ! . . .ለወላድ መሬት ለአድባሩ ።
በርግጥ ብዙ ጀግኖች ነበሩ ።

እናማ ጉበዝ !

ዘንጋኤ . . . የነቃች ለታ ፣
የቀደምቶቹ . . . ውለታ ፣
የቅይሳቸው . . . ትባቱ ፣
የአበሻ ወኔ . . . ፍላቱ ፣

ዘንጋኤ የነቃች ለታ . . .ኢትዮጵያ ዋቢ ስጠራ ፣
"ዘራፍ"- ባይ ከቶ እንዳይጠፋ . . . የእኒያ ባሕርይ ያ
ጮርራ ፣

እዚህ ላይ ነው ቁም ነገሩ ፣ . . .ወኔ ዘራቸውን መጠበቁ
እግዚኦ . . .! ለባለአደራው ፣ . . .ለባለተራው ለጭንቁ

ጦሩ ወርዋሪ ፡- እንዳያጣ ፣
ስንጋው - እንዳይውል ቢጋጣ ።

አንዳደዬ ግን . . .አንዳንደዜ ፣
ብቻ አንዳንድ - ጊዜ ፣

ስንዴው . . . እንክርዳድ ያበቅላል ፣
ርሚጦ . . . ረመጥ ያነዳል ፣
ሰንበሌጥ . . . ገደል ይንዳል ፤

አይቀሬነቱ የማይቀር . . . ዘንጋኤ ያልነቃች ለታ ፣
የዘመን ድጥ የማይቀና . . . መስሎ' ሚታይ የዐይን ቧልታ

እኮ ! . . . አንዳንደዜ
ሸው . . . ሲል - ድንዛዜ ፣
ስንዴው . . . እንክርዳድ ያበቅላል ፣
ርሚጦ . . . ረመጥ ያነዳል ፣
ሰንበሌጥ . . . ገደል ይንዳል ። . . .

. . . ስሚን ልብ ፡- መስማሚያ ይንሳ ! ... እርጉም ነው ተቀባይ ጆሮ
አይታም ያለፈች ዐይን ትደፋ ! . . . .እስኪል ብሌኗ ተነቅሮ

ስንዴው - እንክርዳድ ሆኖ ፣ . . . ስንበሉጥ ገደል - ከናደ ፣
መቅደስ - መቅደላን አርክሶ . . . ገድለ ዶጋሊን ነው - የካደ ።

ስንጋውም - ውሎ በጋጣ
ጋሻም - መካቹን አጣ ።

እንዲያ ነው - ጉበዝ !

ክብረ ኬላዋ ሲሰበር ፣ . . . በማ'ረግ ከልካይ ስጠራ ፣
"አለን" ባይ ከቶ እንዳይጠፋ ... የእኒያ ባሕርይ ደም ጮርራ ፣
ጀግና ያበራው - በጉራብ ፣ አድዋ . . . ማይጨው ላይ ወድቆ፣
ጮራው እንዳይደፈን . . . ዘይቱ ከመቅረዙ አልቆ ፣
እዚህ ላይ ነው ቁም ነገሩ ! . . .ወኔ ዘራቸውን መጠበቁ ፣
እግዚኦ . . .! ለባለ አደራው . . . ለባለተራው ለጭንቁ ።
ጦሩ . . .ወርዋሪ እንዳያጣ ፣
ስንጋው . . .እንዳይውል በጋጣ ።

እዚህ ላይ ነው- ቁም ነገሩ
የሺህ ዓመታት - ታሪክ ዝክሩ ፣

ለዜግነታችን - ክብሩ
እንግዴ ልጁን - መቅበሩ

የጠላት ዕብደት-መግታቱ . . . ቀይ ባሕር ጠበል መንከሩ፣
እዚያ ምጥ ኬላ . . . ."ምጥ - ጥዋ" አናት ላይ መቆሙ፣
ለቀይ ባሕር በር . . . የደንጊያ መዝጊያ መግጠሙ ፣
ጦሩ ፣-ወርዋሪ ሳያጣ
ስንጋው ፣-ሳይውል በጋጣ

18-7-82

ሽው - እልም

እይ . . .!ከማዶ ! . . .ከወደዚያ ማዶ ፣
ደመና ሲከመር - ደመና ተንዶ
የአውሎ ነፋስ ጋራ
ሽቅብ ሲምዘገዘግ ወደ ሰማይ ጣራ ፤

. . . ዛፉን ደግሞ እየው . . . !
ሽው . . .! እልም . . . !
ሽው . . .! እልም . . . !

አሁን ወዲያ ቀና ፣ አሁን ወዲህ ዘመም
. . . ነፋስ ያዋቀረው ፣የአቧራ ግድግዳ ፣
ወደዚያ ሲነዳ . . . ወደዚህ ሲነዳ ፣
. . .ወደዚህ ሲነዳ ፣
ወደዚያ ሲነዳ ፣

ሽው - እልም ፣ ሽው እልም ፣
አሁን ወዲያ ቀና ፣ አሁን ወዲህ ዘመም
ነፋስ ወደ ገፋው . . . ፣
ሽው - እልም - ሽውሽው . . .
. . . ሽው - እልም . . . ሽውሽው ፣
. . .ነፋስ ወደ ገፋው ፣

በቃ ! ልክ እንደዚሁ ነው !
በራስ መተማመን ለሰው ከጐደለው ።

5-5-77

ፉ ጩ ት

እእምሮዬ መንገድ ቢቀር ፡
ባይጨርሰው አሰላስሎ ፡

የሕይወትን ዙሪያ ጥምጥም ፡
የሕይወትን ምርግ አልሎ ፡

ረቂቅ ጉዞ አካሔዱን ፡
ሽቅብ ፡-ቁልቁል . . . ግራ ከቀኝ ማለቷን ፡
የጣምራ ውሎ ሁነቷን ፡
የአንዴዬ - ሬትና ማር ተክለ.ኳን ፤

ጥርሴ ፡- ያልዘለቀውን ስቆ ፡
ሆዴ ፡- ያልቻለውን አምቆ ፡
ድንገት በዘበት ፈንድታ ፡
የአየር - ድማሚቷ ፡

ተፈትልካ - ትንፋሽ ቢጤ . . . ከከናፍሬ ፡
ቀልቤን ይዛው . . . እኔም እውስጤ ውስጥ አብሬ ፡
ፊ ውውው . . . .
ፊው . . .ፊው . . . . .
ያ'ሎሎውን - ምርግ ጥሳ ፡
ዙሪያ ጥምጥሙን በጥሳ . . .

. . . የሐሳቤ ፡-የረቂቁ - ሳይለቅ ውሉ
ትዝታዬን - ከነምስሉ ፡

ካድማስ -

አድማስ -፡ . . .ለሰማያት አጀብ ሁሉ ፡
" . . . ይስማ " ብላ ፡
" . . . ይየው ! " ብላ ፡

ቆላ ደጋው ፣ - ውበት ብርቁ ፣
የለቀቀው ፣ የደቀቀው - ሊቅ - ደቂቁ፣

. . . ገጸ- ነፍሴን ፣
ልል ያልኩትን ፣
እያሳየች አለችልኝ . . . እፎይ በቃ !
አቋራጩ ፡- ያየር ልሳን ፣

ድማሚቷ ፉጨት ሲቃ ።

ፊውውው . . . .

ለመርሳ አባ ዋሸንት

15-3-81

አስቸግርህ ባጣ

በአየር . . . ደንገላሳ ፣
በጫረር . . . የሳንሳ ፣
በነፋስ ትከሻ . . . በገሞራ እስትንፋስ ፣
ልመንጠቅ - እንደዜ ! . . . ስውር ጥበብ ላስስ ፣
ትንሽ . . . ልፋሰሰው ! . . . ዛቴን እዚህ ትቸው ፣
በስማያት ጀርባ . . . በማይገሥረብጠው ።

በል - ንሳ ! - በልልኝ !
በል - ንሳ ! - ንገረኝ !
ማዕበልን - አቅፌ . . . መብረቅን ፣ ጨብጩ ፣
እቶንን - ደርቤ . . . አውሎ - ተጫምቸ ፣
በደመናት - ዋሻ ፣
ውበት - መናገሻ ፣
በነጐድጓድ መንበር፣ . . . ሁሉንም ንገረኝ ... ጉባኤ እንቀመጥ፣
አክናፍ - ወቅኒያት ፣ . . . ይንጠቁኝ ልብነነው. . .ዛቴ እዚሁ ይቅለጥ፣

ልቀቀው ! - አይተንፍግ . . . ታምቆ እስከ መቼ ? . . . ገሞራው
ይፈንዳ ፤
ሽቅቡን - ወደ ላይ . . . ሽቅብ የሽቅቡን . . .እኔነቴን ይንዳ ።

በል - ንሳ ! - በልልኝ !
በል - ንሳ ! - ንገረኝ
መውጫ - ቀዳዳዬን . . . መስኮቴን ክፈተው ፤
ባ'የር - ድንገላሳ . . . . .
በጨረር የሳንሳ . . . አንዴ - ልፋሰሰው ፤
በስማያት ጀርባ ፤-በማይጐረብጠው ።

በደመናት - ዋሻ ፤
ውበት - መናገሻ ፤
የቅኔህ ገበታ - ማ'ድህ ተዘርግቶ . . . በረከትህ ትምላ ፤
ችክ - ያለኝን - ልርሳው፤-ሕይወት ጥላ'ሸትን ...እሾህ አሜኬላ፤
ቅኔ - ሐይቁን ግለጥ ፤- ግርዶሹ ይቀደድ . . . ቅኔ ወይን ይቀዳ፤
ቅኔ - ወይን ጠጥቼ ፤- በፍቅሯ ልሳከር . . . በምስጢሯ ጓዳ ፤
እኔን- ከኔ ልለይ . . . እኔን እኔ ይርሳው ፤
አንዴ - ልፋሰሰው !
በስማያት ጀርባ በማይጐረብጠው ።

በል - ንሳ ! - በልልኝ . . . መደነቅ ትድነቀኝ ፤
በል - ንሳ ! - ንገረኝ . . . ልገረመውና ነፍሴ ፋታ ታግኝ ።

ባ'የር - ድንገላሳ ፤
በጨረር - የሳንሳ ፤
በደመናት - ዋሻ ፤
ውበት - መናገሻ ፤
በነፋስ ትከሻ . . . በገሞራ እስትንፋስ ፤
ልመንጠቅ ፡- ! አንደዜ . . .ስውር ጥበብ ሳስስ ፤
ትንሽ - ልፋሰሰው ፤
በስማያት ጀርባ በማይጐረብጠው ።

ለአቶ ጸጋዬ ገ. መድኅን
የተበረከተቸ ።

6-1-82

" ኮከቡን "

የሰማያት ጀርባ - የከዳው ኮከብ - ማታ ድንገት
ሊሆን የአጀባው ጭዳ - መሥዋዕት . . .

ጥንቱን - ከነበረበቱ ፥
ከብልጭ ብልጭነቱ ፥
ከስሞ ወደ አልነበረበቱ ፥
ከውቅር ቅምጡ - እንዲከላ ፥
የአንቀልባው - ቋጠሮ ሲላላ ፤

የሰማያት ጀርባ - የከዳው ኮከብ ፥
ባለ ተራው ለሥራት ግብ

በጠፈር ጀርባ - ምጣድ ውሎ ፥
ተለብልቦ - ተንገዋሎ
ግሎ - ከስሎ

ከቅምጡ - ወደ ሞቱ ፥
ፍጹም - ወደ'ማያቁቱ ፥
በጠፈር ቱሽ - ተገፍትሮ ፥
ይሰወራል እያበራ - ተቀጣጥሎ ፥
ለሰማይ ገጽ ጌጡን - ጥሎ ።

እንደምነው - ድንቅነቱ -!
ጌጥ የሚሆን - ሞት መብራቱ ።

29-3-82

ብቻውን . . . !

. . . ብን . . . እብስ
ብን . . . እብስ

ከጥላ ተጣልቶ . . . ከራስ ተሰራርቆ ፤
ከራስ ጠረን ሸሽቶ . . . እስትንፋስን ርቆ ፤
በመብረቋ ደቆ ፤

ብን . . . እብስ
ብን . . . እብስ ፤

ሺህነትን ገሎ . . . እልፍነትን ቀብሮ ፤
ሺህ ሙታንን ሆኖ . . . ገሃነሟን አጥሮ ፤
በሙታን ከተማ -
ኖሮም - ያለ መኖር . . . ነቅቶም የማይሰማ ፤

ብን . . . እብስ
ብን . . . እብስ ፤
ሌት ቀን . . .ደንብዞ
በ'ጣ ተክሏ መሮ . . . ሕመሟን ደንዝዞ ፤
ማመን -
መተማመን -
ቅዠቷን . . . ደንግጦ ፤
ቀጋ ጡቷን . . . መጦ ፤

ብን . . . እብስ
ብን . . . እብስ ፤
አለኋችሁ ላይል . . . አለሁ ባይም አጥቶ ፤
ጠሪ ባያገኝም . . . እሱም ለወይ ታክቶ ፤
በሰው ጫካ መሐል . . . ቀልብያው ሸፍቶ ፤

የመሐል አጠገብ . . . እሩቅ ተሰውሮ ፣
ባይተዋርነትን . . . ሰቀቀኗን ነፍሮ ፣
ነጠላውን ቀዞ ፣
በቅንዓት . . . ነብዞ ፣

ሌላ ምንም አይደል !

ታሽቶ - መታሸቱ ፣
ብን . . . እብስ ማለቱ ፣

ብቻው ፣ብቻ . . .ሲቀር ፣
ብቻ ሲቀር አይደል !? . . .በብቸኝነቱ !

20-11-82

ከተከርቸም

ሲቻቻሉ . . . ተቻችሎ ፣
እንጂ ፥- ሲቻቻሉ . . . ተሸናግሎ ፣
መቸም ቢሆን . . . ሃይማኖቱ ሳያረገው ፣
ጀርባ - ከሆድ . . . የሚጋደም ምን እንጀት ነው ?

እንግዲህ . . . ምን አረጋለሁ ?
ቀኔን በከንቱ . . . ፈጀሁ ፤
አንቺም ፥- በመረጥሽው . . . ንጉጅ ፣
እኔም ፥-መንገዴን . . . ላብጅ ።

ካሁን ወዲያ - አንቺን ባልሆን ፣ . . .እኔን - ባትሆኝ ፣
ባንድ ብልጠት - ቀናሁብሽ ፣ አንቺ በኔ - ባትቀኝብኝ ፣
የሞት አፋፍ ፥- ንስሐ አይደል !? . . . ከሚበላኝ ልናገረው ፣
ባይሆን አንቺ ፥- እንዳመልሽ . . . ሰምተሽ እርሽው ።

"... ሰው ፡- ሕሊና ያለው ... እንስሳ ነው - ይባላል ፤
ሕሊናውን ከገደላት ... 'ከብትነቱ ብቻ' ይቀራል ።
አንቺም ፡- ሕሊናሽን - ገድለሽ ፤
ስብዕናሽን - ከተውሽ ፤
ምንኛ ቆንጆ እንስሳ ይወጣሽ ! ! "
በይ -! ሻንጣዬን
አቀብይኝ ።

ትዝታ

የዘመን ከታብ ብራና ፤ ... የደበዘዘ ፊደሉ ፤
የሕይወት እልፊት ጥምጥም ... መኖር - ሃሌታው ጥቅልሉ፤
በሕሊና ንባብ ሲፈታ ... የጊዜ ወገብ ቀበቶ ፤
የትዝብት ዐይን ... ወደ ኋላ ተመልክቶ ፤
የዕድሜ ወንዝ ከጅረቱ ... የቀበረውን ሲተፋ ፤
ትውስታ ባይምር ሲሣል ... መለሎም ይሁን ጎልዳፋ ፤

በሐዘን በደስታ ... የስሜት ጭፍራ ታጅቦ ፤
ትዝታ ትዝ ሲሰኝ ... ከማከማቻው ተሰብስቦ ፤
ቀልብ ቀናትን - የኋሊሽ ስቦ ፤
— የኋሊት ጋልቦ ፤

ያለፈን ጊዜ ሲመለከት ... በራሱ ባቡር ተሳፍሮ ፤
- ዙሪያ ጥምጥሙን ዞሮ ፤

ሰው ፤—

· በለሰለሰ እንጉርጉሮ ... ዐይኑ በእንባ ሞልቶ ፤
· ልብ በሚሰውር ፉጨት ... ወይም ዋሽንት ተጫውቶ ፤
· ክራር በገና ደርድሮ ፤
· አሊያም በመሰንቆ ዘምሮ ፤

. ትዝታውን ይገልጣል ፣
. አሁን ላለው እሱነቱ . . . ነበርንን ያጫውታል ፤

አንዳንዴ ግን ትዝታ ፡- ትንታም አለው አሉ ፤
ብስባሽ ምሬት ሲታሰብ ፣

የኑሮ ውጣ ውረድ . . . የሰቆቃ ደለሉ ።

21-1-77

ሽምቀቃ

ቀጭን ፡ . . .ጭራ ነገር ፣
ተከትዬ ፣
እንደ ጭራ ቀጭን ፣
ሙጥኝ - ብዬ ፣
በሆነች ነገር - ማነቆ ፣
ከቅጥነቷ - ተናንቆ ፣
መዳፍ ፡- መጨበጫዬ . . .ተሰንጥቆ ፣
ብፈታውም - ያመኛል ፣
ሕመሙም - ደስ ይለኛል -።

ስለቷ ፡- ቀጭን ጥበብ ድር መታሪ ፣
ስበቷ ፡-ሙት አስደንባሪ ፣

መተልተል - ይወደዳል ! ?
ሞተ ነፍስን - ይጓደዷል ! ? . . .

የመጠማመዴ
ከቀጭኔ ፡-

እንደ እማዬና . . . የሙ'ዳዋ አድሩስ ፣
እንደ ቀልቧና . . . የጋቻ ላይ ጭስ ፣
ከጣራም በታች . . . ከጣራም በላይ

እጅግ ... ወደ ላይ !
ቀጭኔ ቀድማ ... ስትመለስ ...
ተከትያት ፡ ... ገበስበስ - በስ - በስ ....

“... አይጨብጡም ፡
አይለቁም - ከተጫበጡም ...”
ብዬ ፡- ሙጥኝ ብዬ ፤
ጭራ ነገር -ተከትዬ ፤

ገበስበስበስ ....
ስንደባበቅ ... .መጠጋጋት ፤
እየተጣጣንም ...ባብሮነት ፤
በተቃርኖ - አንድነት ፤
ባንድም - ተቃርኖነት
እንደ እማዬና - የሙዳ'ዋ አድሩስ ፤
እንደ ዐይኗና ፤
እንደ ቀልቧ ፤ ...የጋቻ ላይ ጭስ ፡

ቅኔ - ወላላይቱ ፤
ቅኔም - መሪኸቱ ፤
ባንቺ የምገልጠው ... ሕይወት ማኅደሩ ፤
ሥጋትም ፡-
ናፍቆትም ሆነና ነገሩ
ቅጥ - አጣሁለትኝ ፤
ቅጥ የለውም ምትሩ ።

መድማት ...ይወደዳል !?
ሙትን ...ይጓደዱል !?

... ሳመርም - ባልቆርጥ ፤
ስብሬም - ባላመልጥ ፤
ባጣልሽ ጊዜ ቅርጥ ፤ ...

ሕይወት ፣ . . . ብትሆን ቅኔ ፣
የኔም ነገር . . . .ቅኔ ፣
ቅኔም ደግሞ . . . . እ'ዱኔ ፣
ተዘባረቁብኝ . . . አዘበራረቅሽው ፣
ጠፍተሽ በጨበጥኩሽ . . .ስውሬን በያዝሽው ።

21-11-81

ቅኔ - አይደለም . . . ! በለኛ

ክፍል አንድ

መኖር አጅሬ

ተናውጣ . . . . . እንዳልረገበች ፣
ደፍርሳ . . . . . እንዳልጠለለች ፣
በየዱሩ ፡- በየዕለት - ገጠመኙ ፈፋ ፣
ትኑር እንጂ - ተንከራታ - እየባዘነች ጉርፋ ፣
ቃል ! . . . ባየውም - በማልዳስሰው ስማይ ፣
ቃል ! . . . በመደዴ ፍጡራን ፡- የናንተ የናንተ ሲሳይ ፣
ቃል ! . . . ችላኝ - በቆምኩባት ምድሬ ፣
ሐቄንስ - አትጨልጣትም ፣

'ውነት ! . . . . መኖር አጅሬ ።

መቸም ፡- የሕይወት ምስጢር ጉራንጉር
የዕጣ ድልድላችን ነገር
ዐይንን ፡- በተቃርኖ . . .አንድነት ሴራ - አሳብዶ ፣
ከሕመሙ ፡- ትፍስ'ት ቢጤውን አዋልዶ
ጥርስ ላይ እንባ ለብዶ ፣
በአንጀት - አንጋሎ ፣
በጀርባ - አቁሞ ፣

ባዶ - ለባዶ ፥
አናግዶ ፥ . . . .
-"ኑሮ"- ያለው ፈሊጡ . . .ቢያወሩት አይቸክምና ፥
ቢዘርፉት አያልቅምና ፥
መልሼ - ደግሞ ላውራልህ ፥
መኖር አጅሬ ፡- ይኸውልህ ።

ይኸውልህ
የምልህ . . .

ውስጥ ውስጤን - እያባተለኝ ምስጢሩ ፥
እንደ ጥጥ እያባዘተኝ ፡- ከንክኖት ልቤን ነገሩ ፥
ውስጤ ፡- ተዳፍኖ ፥ በግኖ፥ - እንዳይጋጋም ፈርቼ ፥
ልተነፍሰው ፡-ከጀለኝ ፡- ንዳድ ረመጡን አውጥቼ ፥
የማይሆነውን ፡-
ያልሆነውን ፥
እንዳይመስልህ ፡-
የምነግርህ ፥ . . .
"ሕይወት " ቅኔ አይደለም ! ? - እንዳትለኝ ፥
በጥበብህ - ባትገድበኝ ።

እስቲ - ላሳይህ ፡- እየውማ ! . . .የኛ'ኛን ሜዳ ጓዳ ፥
ገሃዱን - ምስጢር አድርገን ፥ ስናይ ፥ ስንዝቅ ፍዳ ፥
ደሞም ፡- ደቃቁን - አኩርተን ፥
ሳናውቀው - ምስጢሩ ታይቶን ፥
አዕምሮአችንን - እሆድ ከተነው ፥
ሁሉን ፡- " በሆድ አምሳል " ስንቀርፀው ፥
ሕሊናችንን ክደናት ፥ በሥጋ ወህኒ ተጠፍራ ፥
ሆና ! - ለግዑዝ አካላችን ጭፍራ ፥
ባሕሪያችንም - ተሸቅጣ ፥
ገደብ አልፏ- ተማግጣ ፥

የተንከላወስንበት . . .ያ- ዘመን . . . ሲነሣ በወግ ተርታ ፥
የሸለቆ ጉም መልኩ ፡- እየተለዋወጠም ቢምታታ ፥
'ውን ቅዠትን
ያተኩራል ፥
መደንበርን - ተደንብሮ ፥
ገልቱነትን - ተኮርኩሮ ።

ታዲያ ፡- እውነቱ ቃሉ ፤
ምንነታችን ፡- አሻራው . . . ያመረርነው ሐቃችን ውሉ ፣
ሕቅ . . .! ይለኛል ፤
ስቅ . . .! ይለኛል ፤

ሳስታውሰው -፤
እኔነቴም ፡- ይታመማል . . . ወግ ነው ብዬ ስተርተው ።

ሕሊናዬን . . . የዋሸሁት ፤
ያጐደፍኩት . . . ያሳደፍኩት ፤
ያነገልኩት . . . የሸፈንሁት ፤
እኔነቴን ፡-የገደርኩት . . . የሸሸሁት ፤
በመምሰል ወግ ተደልዬ . . . ውስጤን መልኬን-የጋረድኩት፣
እንዳ ድባር-ቂጣ ቀብቸው . . . ያልሆነውን ያስመሰልኩት ፣
ከውስጤ እየታገለኝ . . . እንደ ሽል ይገላበጣል ፤
የተገነዘው፡- ደመ ነፍሴ . . . ራሱን ሊወልድ ያምጣል ፤
በደረቅ ቁንጢጥ ሸንቁጦ . . . ግዛጼው ኃያልነቱ ፤
ይፋጃል ፡- ይቀጠቁጣል . . . የጸጸት አለብላቢቱ ።

ታድያማ ! . . . . ምንነት - ከውነት ተጋፍጦ ፤
የትውስታን - ደመና መጦ . . . ሲያወጣው አጉመጥምጦ ፤
ይህን ፡- " ቅኔ አይደለም !" . . . በለኛ !

መለኛ !

ይኸው ፡- ምንነት ያልኩህ - ከውን - ውነታ ተጋፍጦ ፤
ያደመነንን - ደመና መጦ ፡- ሲያወጣው - አጉመጥምጦ ፣
ምኔም - ገድቦ አያቆመው ፤
ልጓም ፡- ክንብንባችንን ሲያፈርሰው ።

. . . ዘልቆ - የሠረፀውን . . . ልቡናችን አሜን ያለውን ፣
ሲራቆት - ያየነውን ፤
የኛነታችን - ቀጥታ ፍች . . . መግለጫ ቋንቋ ሳጣ ፤
ዘይቤዬም - ተምሳሊቴም - አነነቻ . . . ቃሌ ከትናጋዬ ተቆ
ራርጣ ።

አሄሄ . . .! የኛማ ነገር ፡- የኛ ኑሮ ሜዳ ጓዳ ፤
የገሃድ ምስጢሩ ፡- የደቃቅ ግርድፉ ዘያዳ ፤
ያለውል - የባከንበት ፍዳ ፤

ላንሾልከው - ያበጀነው ቀዳዳ ፡
እንዲህ - ተራቁቶ ሲያራቁተኝ ፡
ፌጦ - ገበናው ሲያጋልጠኝ . . . . ሰቀቀኑ እንዳያንቀኝ፡
ያርደኛል :- ማዬት መስማቱ ፡
አመልጥ ስል :- ከራስ በራስ ዳኝነቱ ፡

. . . ልኬን የማወቄን ያህል . . . . ልዝብ ወኔዬን - አባብዬ ፡
እየቀዘዘኩ . . .እህ .ህ.ህ. እያልኩ ፡ ጭብጥ ብዬ ፡
እንዳልደፍራት . . . በሩቅ ሆኘ ፡
ስትገልጠኝ . . . ተሸፍኘ ፡
አማልክትን . . . ለረድኤት ተማጥኘ ፡
ካልበቃሁት . . . ተገልጩ ፡
ካልጨረስኩት . . . አዳምጩ
ካልዘለኩት . . . ተረድቼ ፡
ካልፈጸምኩት . . . ጉድ አውግቼ ፡

. . . ይኸን :- የኛን - ሜዳ ጓዳ ነገር ፡
የሕይወት ምስጢር ጉራንጉር ፡
ዘርፌው - ካላለቀ . . . ነግረውኝ - ካላለቀ ፡
ስሜቴን - ካዘበራረቀ ፡
ይኸንም - " ቅኔ አይደለም " - በለኛ
መለኛ !
መለኛ !

መቼም :- የድልድላችን ነገር ፡
የሕይወት ምስጢር ጉራንጉር ፡
ከሕመሙ :- ትፍስት ቢጤውን አዋልዶ ፡
ዐይን ላይ - ሣቅ አዋዶ ፡
ጥርስ ላይ - እንባ ለብዶ ፡
በአንጀት - አንጋሎ ፡
በጀርባ - አቁሞ ፡
ባዶ ለባዶ
አናግዶ . . .

ካየኸው ዘንዳ እስከ ዛሬ ፣
መኖር አጅሬ ፣
"ቅኔ - አይለም" -በለኛ!
መለኛ !
መለኛ ።

ለተሻገር ሽፈራው

17-7-81

ክፍል ሁለተ

ደመውትስ-ካላለቀ?

ስቧ ፡- ነፍሴ - ከጥልቀቷ ፣
ከሲሶዋ ፡- ከድርበቡ - ከሌማቷ ፣
ማስና ፡- ባዝና ፡- ጥራ ግራ ፣
ብርሃን ብታይ - ተደናብራ ፣
ያፈጠጠው - ሙት ውነቷ ፣
የመባነን - ስቅቃቷ ፣
የተጠየቅ - ክርክሬ

ይኸውልህ !
እንካ ዛሬም - መኖር አጅሬ !

እንደ ቆመ ፡- - ቆሞ'ማይቀር . . . የነፍሴ ነውጥ፡- የማዕበሷ
ደንገላሳ ፣
ከሕይወት ጋን ፡- ከዕድሜ ምንቸት . . . ለማቃመስ ፡- ቀነናንሳ
አቆይታን ፡- ቆይታለች - ተጠየቁ ክርክሬ ፣
በዳኘነት - ! በመንፈሱ !
ባፅመ ድዱ - ! . . .ተደኘኛ - መኖር አጅሬ ።

ሌላው ይቅር ፡- ከኑሮው ጋን ከቅናሹ ፣
እኔም አንተ ከሰለልነው ፣
መንታ ማወቅ ከምናውቀው ፣

እስቲ አስባት ያቺን ጐጆ - የዚያን የሰው ።
አንዷን -
አንኳን ።

ያቻትና . . . እዚያ ማዶ :- ጐጆይቱ ፣
እጐጆው ውስጥ :- አለች ሚስቱ ፣
ያቺ ሚስቱም :- ሁሉን ሆና - ሁሉን ነገር የሆነችው ፣
የሱን ገላ በገላዋ - ለብሳው ለብሷት . . . የሞቀችው ፣
በሷ ጥልቀት አስገብታው . . . .የሱን ጥልቀት የገባችው ፣
ጐደሎዋን የሞላላት . . . . ባዶነቱን የሞላችው ፣

እያወቃት - የራበችው
አጣጥሟት - የጠማችው ፣
አዋህዶ - እንደ ሠራት . . . . አዋህዳ የሠራችው ፣
መከፋቱን - አልቅሳለት . . . ለደስታው የሣቀችው . . .

እሱ ማለት :- እሷ አይደለች-!
አልነበረም . . . ግርድፍ ቋንቋው ፣
አረጉታ ፤ እሱን ማለት - እሷ ሆነች ፣
ምን እንበለው ?
እሷም ማለት :- እሱ ሆነ ፣-ምን ያድርጋት ፣
ምን ታድርገው ?
አካል - ላካል ፣- ነፍስ ለነፍስ ፣- ተነሣሥተው ።

ደሞ አንዳንዴስ --- - በዶል ሲያቁር ፣
የጮኸ'ለት በሹክሹክታ ፣
የነሱነት ድንግል --- - ትርጉም ፣
በድንገቱ ስትገፋ ፣- ድንገት ውስልት ተወስልታ ፣
ማፍቀር ሐሴት :- ፍቅር ፣ ውበት ፣-ጠቧት ቦታ ።

መገሰሱ :- የተሣነው ፣
የባከነው :- ልቦናቸው ፣
ሲተዛዘብ :- እርስ በርሱ ፣
ድንግልና - ሲካሰሱ ፣ ድንግልና ሲዋቀሱ ፣

ልሳናቸው ... የራሳቸው ፤
የግላቸው ... የነበረው ፤
በዳፍንቱ ... ቃሞባቸው ፤
ሲቃመሙ ... ሲቃመሙ፤ .. ሲቃመሙ ፤ .. ሲቃመሙ.
ሲደምጡ ... ሲደምሙ፤ ...ሲደምሙ፤ ...ሲደምሙ ..
ሲደምሙት - ካላለቀ ፤
ስሜት - ካዘበራረቀ ፤
"ቅኔ - አይደለም" - በለኛ
መለኛ !
መለኛ !

ለነዘነበ
21-7-81

ክፍል ሦስት

ይኸንሳ ! ...

..."እሰይ ነጋ !" ... ማለቴ እርግጥ ...ስትወጣልኝ በማለዳ
ለዕለት ግብሬ ስሰናዳ ፤
የእንጀራዬን -
የግዳጄን -
ስትጠልቅም ..."መምሸቱ ነው" ...ሁሌም ላለሁ ፤
አመሻሼን እያሰላሁ ፤
ረዘመ - ጥላ አጠረ
ዋሪ ሲሆን - ቀን ቀተረ
ዛሬዬን - ከማሰላሰሌ - ቀኔን ከመቁጠሬ ሌላ ፤
ጉርሻ - አትለኝ ፤ ፎሌ ጠላ ፤
መቼ - ገብቶኝ ...? መኖር አጅሬ !

የፀሐይ ገድል ፍካሬ ።

ግና - ይኸ - የአጠገቤ . . . ጅልነቱ ልጅ ያረገው ፤
ቆቧን ጥላ ፤—
ብቅ ስትል በማለዳ . . . ፈገግታዋ የሚያፈገው ፤
የሌለውን ፡- እይ እያለ ፤
በዐይኖቹ ፡- እያጣቀሰ . . . በጣቱ' የጠነቆለ ፤

" . . .ውበት ይሏል ይህ ነው . . ." ሞፎ . . .
ተስፋ ፡- በወርቅ ቀለም . . . በእምብርቷ ከናፍር ተጥፎ ፤
ዙሪያዋ - ዳግሞ ለዛ ነው . . . በድዱ የሚስቅ ጨቅላ ፤
ድድ-ሲበቅል ያማል-ሞፎ ! . . . ጨረር ዐይን እንዲያቀላ ፤
እስቲ-ወደላይ አቅና-ሞፎ ! . . . ያየኸው ሰማይ ጉልቷ ነው ፤
ዘግይታም ታደምቀዋለች . . . ጥራት እንድያነቱን እንኩራው፤
የማታም ግብሯ - ሞፎ ! . . . ሰላም ይሉታል ፤

. . . እርጭታና ፍጻሜ ፤
የምሉዕነት ተምሳሌት
. . . የግብ ተክሉ ድምዳሜ ።

ሞፎዬ ! - አይ ሞፎዬ ፤
ምስኪን - ሞፎዬ ፤

የሚለኝ ፡- ይኸውልህ - የአጠገቤ ፤
ተጠበብ ሲል - በጥበቤ
እየው ይኸን . . . የአጠገቤ . . .ለከንቱ ዕጣው - ታማኝነት ፤
ተጠበብ ሲል . . . በጥበቤ . . .ውስጤን ድፍኔን-የሚዳራት።
ምነው ሸዋ . . .!

*

ለምን ይሆን ? . . . መጨነቁ ፤
ከብቻው . . . መተላለቁ ፤
ምንድን ይሆን ? . . . መላቅጡ ፤
ከብቻው ብቻ . . . መቃለጡ ፤

ከግዑዛን . . . መነባነቡ ፤
ከ'ህል ውሃ . . . መናጠቡ ፤
ወደ ሆዱ . . . እንባ አንብቶ . . . በእንባው ዶፍ መታጠቡ፤
ወደ ውስጡ . . . ተስረቅርቆ . . . በንባው ናዳ መጠረቡ ፤

ለከንቱ ዕጣው - ተደልሎ ፤
ሳንወክለው - ተወክሎ ፤
ከአየራት - መላተሙ . . . ለደመናት መንሰቅሰቁ ፤
በወፍ ፍቅር - ተገንድሶ . . . ለአበቦች መፈንደቁ ።

ታዲያ ይኸን :- የየአንዳንዱን - የጧት ቁንጥር ፤
የሕይወት ምስጢር - ጉራንጉር ፤
ካልዘለኩት . . . ተረድቼ ፤
ካልጨረስኩት . . . ተሰምቼ ፤
ካልፈጸምኩት . . . ጉድ አውግቼ
ዘርፌው - ካላለቀ . . . ነግረውኝ ካላለቀ ፤
ስሜት ካዘበራረቀ ፤
ዛሬም - « ቅኔ አይደለም - ! » በለኛ !
መለኛ !
መለኛ !
መለኛ !

6 - 8 - 81

ክፍል አራት

ስብጥርጥር

የሰበዝና . . . የአክርማ ጥማድ
ወስፌው ግን . . . በስፌው ክናድ ፤

ተምሳሌት ነው . . . የእስስራችን ምሳሌ ፤
ውበት ከስቅቃት አለላ . . . ባንድ አለፍነት ጉራማይሌ ።
እኔና አንተ - አንድ ነን ፤
ቃል ከሥጋ - ነስተን ።

አንዳቹ "ሹክ" . . . አለኝ ዛሬ
መኖር አጅሬ !

እኔና - አንተ - አንድ ነን ፨

አንድም -
አይደለንም ።
በሕይወት ጉዞ ክልንውስ . . . በምስጢሯ ጉራንጉር ፤
የየድልድላችን - ድርበብ ስፍር . . .

የስበዝና የአክርማ ጥማድ ፤
ወስፌው ግን - በሰፊው ክናድ . . .

መሆኑ ብቻ ፦

ከቅኔም ባይጠላለፍ . . . ከቅኔነቱ ባይለጥቅ ፤
ለተራም ስላቅ አይሰምር . . . ድድ ግልፍጫም አያደምቅ

. . . አንዳቹ' ሹክ' አለኝ ዛሬ ፤
መኖር አጅሬ . . .
. . . የእስስራችንን - ምሳሌ ፤

ውበት ከስቅቃትነቱ . . .በአንድ አለፍነቱ ጉራማይሌ
የኔና የአንተም . . . የአንድነታችን ድንበሩ ፤
እነ - እንቆቅልሽ ቤት ነው - አዳሩ ።
ግፋ ቢል ።

ለመብራቱ ገበየሁ
9 - 12 - 82

ዘላለማቸው

አንተም የዘላለሙ !

እንዳ'ማኒው - እንደ እምነት ፤
አዛዡ - ለየ ሕይወት ፤
ሊግቡ - ወይ ለውድቀት ፤

አንተ ነህ ሲሉ - ያማሉ ፤
ሰዎች - ሁሉ ።

ካለህ ታዲያ -ጸጥ አትበል ፤
እሳት የለውም - ከሰል ፤
ጸጥታው ።

ሕይወት ብርቱ ሰልፍ ነው ውጊያ ፤
የእሰጥ አገባ - ፍልሚያ ፤

ሰው መሆንስ የማያምረው ፤
ማን ይገኛል ?ካለስ ማነው ?
በጉዳና ላይ ትርምሱ -

በ'ሰጥ አገባው - ያለፋይዳ ፤
አምሮታቸው -ሳይጎዳ ፤

በሰው መሆን - ምኞታቸው ፤
" ወዴት "- ለጠፋባቸው ፤
እባክህ - አሳያቸው ።
ለየአማኒው - እንደምነታቸው ፤
እባክህ - ንገራቸው ፤
ዘላለሙ - ዘላለማቸው ።

26 - 6 - 82

አይሻልም ?

ያወራነው ፣ የመከርነው ፣
የተለምነው ሁሉ መሠረቱ ፣

መሐላችን ፣ የዕቅዳችን ፣
የልባችን ዜማ የትናንቱ ፣

መሆን ቀርቶ ፦ መምሰል ሳይሆን፣
በ'ጣ ወይ በአጋጣሚ ተይዞ ፣

በሁኔታ ፦ " በተጨባጭም " - በሉት
በሥራዬም ቢሆን ደብዝዞ ፣

ብቻ - በማናውቀው አንድ ፈቃድ ፣
እግር ተወርች ተቀፍድዶ ፣

የምናውቀው ትዝታ እንኳን
ከእሳቢያችን ተቃቅሮ - ተገይዶ ፤

ፈቃዳችን ፦ የት የለሌ - ከአድማስ ማዶ ፣
ስኬታችን ፦ ሲሆንብን እዚህ ማዶ ፣

የስኬት የክንውን አዙሪቱ ፣
የጊዜ ነውና ዳኝነቱ ፣

ፍርዱን ለጊዜ ትቶ
ይሻላል መስል መርሳቱ ።

አይሻልም ?

19 - 11 - 79

ምስክር ፍለጋ

ከውሸት ድሪያ ሰቀቀኑ ፤
የስማያት ዕጣን መማጠኑ ፤
ከአግቦ ሱስ ዐመል ልክፊያ ፤
ከስንቱ አሉባልታ ጥልፊያ ፤
ከሸብረብ - ሽር ጉዱ ፤
ከታይታ ግልቢያ ወጥመዱ ፤
ከይምሰል ጣቅ ግልፍጫ ፤
ከሕሊና ክስ ቁንጥጫ ፤

ጸጥ - ረጭ ማለቱ ፤
ከኔነት ሽሽቱ ፤
ዝም ጭጭ ማለቱ ፤
ከአበሳ ሥጋቱ ፤
ጭው - እብስ እንደ ቀልድ
ከሐሳብ ውጣ ውረድ ፤
ሲጥ - እልፍ ለአንደዜ ፤
ከሕይወት ድንዛዜ ፤
እንደሚሻል - የቱ?
ባወጋልን ሙቱ ።

እዚህ ብሉ - ጠጡ ፤
ከዚያ ንጡ - ገርጡ ፤
እይህ ፍቅር - ወርዶ ፤
እዚያ ቁጣ - ነዶ ፤
እዚህ ዳዴ - ገና ፤
ማዶ እልፍ - እርጅና ፤
አሁን የጣቅ - ድባብ ፤

ወዲያው - ያዘን ድብዳብ ፥
የትናንት - ዝማሬ ፥
ኑዛዜው - ለዛሬ ፥
ድው ! - ሲል ሁካታ ፥
ግም - ሲል እርጭታ ፤

ከዚህ ድግግሞሽ ፥
ከሕይወት እንቆቅልሽ ፥
ጾጥ - ረጭ ! ሥርፀቱ ፥
ከኔነት - ሽሽቱ ፥
ዝም - ጭጭ ንግሡቱ፥
ከአበሳ ሥጋቱ ፥
ጭው - እብስ እንደ ቀልድ ፥
ከሐሳብ ውጣ ውረድ ፥
ሲጥ - እልፍ ለአንዴዜ ፥
ከሕይወት ድንዛዜ ፥
እንደሚሻል የቱ ?
ባወጋልን ሙቱ ።

6 - 13 - 75

ማቄ ያሥቀኛል

ሳላየው - በቅጡ ፥
ቀኑ - መሸምጠጡ ፥
ወሩ - መፈርጠጡ ፥
ሸበት - መፈርቀጡ . . .
- ያሥቀኛል ፥
መልሶም ማቄ ያሥቀኛል ፥
በማቄ እሥቃለሁ ፥
ማለት ነው ።

ንባብ

ነጥብ . ከነጥብ . . . . ቅርጽ ከቅርጽ ተሰካክቶ ፣
ዐይንም .ግዑዝ ምልክት ተመልክቶ ፣
ቃል ከትናጋ - ሕያው .ቃላትን አውጥቶ ፤

ሕሊና ባንድ መልክት . . . ተኮርኩሮ ሲነካ ፣
አንጀት ሲረሰርስ . . . የነፍስ ጥማት ሲረካ ፣
የንባብማ ዋጋ በምን አምሳያ ሊለካ ።

ሰው ቁጭ ብሎ ከቤቱ ፣
ያለም ዙሪያን ዳስሶ ማየቱ ፣
የሐሳብ ምንጩ ጥራቱ ፤

በአእምሮ - ጉልምስና - ስለቱ
አፍራለት - ሥጋ አካል ምስኪንነቱ ፣
አደባባይ ውሎ መግባቱ ።

በዕድሜ - በሥራ ፣
በሩጫ - በበረራ ፣
የስንት ድካም አዝመራ ፣
የውነት ቀዘፋ ማኅደር ፣
የትርጓሜውን ቁም ነገር ፣
በር ቁልፉን ለመስበር ፣

በአቋራጭ ለመንደርደሩ ፣
በውቀት ጥላ ሥር ለማደሩ ፣
ከጕዳናው ሁሉ አጭሩ ፣
ከፊደል - መመሳጠሩ ።
ከወራት ካመት ተሚግቶ
ከረምት - በጋን ደጅ ጠንቶ

በስልፍ ወረፋ ሳይጋፋ ፤
ከምናብ ለመጣለፉ ፤
የንባብማ ጥቅሙ . . .

አቤት . . . ! ሀይ - ሀያት - ነበር ።

ደረቅ ሐቅ መጋቱ ቢቀር ፤
ደረቅ ሐቅ መጋቱ ቢቀር ።

7 - 7 - 1977

እስ - በሱ

ሰው እንጂ - ቅመሙ ፤
ጉዳይ - ጉዳይ ሳይሆን . . . ጉዳይ ማስታመሙ ።

ሰው እንጂ - ወለላ ፤
ሐሳብ ጠኔ ሲሆን - ረኃብ የሚከላ ።

ሰው እንጂ ደመና . . . ሰው እንጂ ዝናቡ ፤
ነገር ማለዘዙ - ጥልን ማለዘቡ ።

ሰው ለሰው
ጭዳ - ነው ።

ደሞ - ሌላም አለው ፤
"ሰው መቸም - ብዙ ነው"

አልፎ - አልፎ ከውስጡ ፤
ሰው - በመሆን ቅጡ ፤
ሲያውቅበት መጎድጎድ . . . ሐቅን ሊቀብርበት ፤
ሊተናኮልበት . . . ሊጠማመድበት ።
እና ሌላ - ሌላም ፤
በጣም ሌላ ሌላም !
ሌላ ሌላ - ሌላም !

27 - 6 - 79

ላታውቁበት

. . . ቅጥሩ አይደለ . . . ከቅጥራችሁ ፡
ውልዱ አይደለ . . . ከውልዳችሁ ፡
ይጥፋ ፡-! ተዉት . . . እባካችሁ ፡
ይፍዘዝ - ተዉት . . . ባምላካችሁ ፤

. . . እሱ ሌላ ! . . . ብኩን ኬላ ፡
ሥራው ሌላ ! . . . ጉም አዘላ ፡

ውበት - ዘሪ ፡
ውብ - አዝማሪ ፡
ውበት - ወዳጅ ፡
ውብ - አሳዳጅ ።

ከቅሬው ፡ ደንብ . . . ወጣ ብሎ ፡
ከጨጎጎት . . . ከቁጥቋጦ ፡ ተማምሎ ፡
ቤተሰቡን . . . . ባልንጀሩን . . . . ውሽሚትን . . . ችላ ብሎ፡
ቅጠል ሣሩን . . . ጭሳጭሱን . . . . ግብሩን ከፍሎ ፡
በቃምቡራ - ተለማምኖ . . . . ሲኦል ወርዶ . . . ገብቶ ወጥቶ ፡
ደመነፍሱ - ተግ ! . . . ስትል . . . ከኑባሪያት - እኩል ተግቶ፡
እርገረማው ፡ ተቦጭቃ . . . . ከአዲስ ሕልሙ - ተንጸባርቃ፡
ወደ አርያም . . . ነፍሱ መጥቃ ፡
ደመነፍሱ - ተግ . . . ! ስትል . . . "ቦግ እልሚት" . . . ስትበራ
ሲካካውን - " ደፍቶ - ረክቶ " . . . አውራ ዶሮ እንዲያቅራራ

. . . የሱን መኖር - ልዕልና ፡
የራዕዩን - እርግዝና ፡

. . . ከቀላያት . . . ቃል አዝንቦ ፡
እሳት ፊደል . . . ጭሮ ከትቦ ፡
ነዶ - ፍሞ . . . ረመጡን ለኛ አሙቆ ፡

የሙጥኙን . . . " አለሁ " - ይላል ፤
ሒድ ! . . . ቢባልስ - መች ይሔዳል ፤
ሙት ! . . . ሲባልስ - መች ይሞታል ፤
አትነካኩት - እባካችሁ !
ወልዱ የለም - ከደማችሁ ።

. . . እሱ - ሌላ . . .! ብኩን ኬላ ፤
ሥራው - ሌላ . . .! ጉም አዘላ ፤
ውብት - ዘሪ ! - ውብ አዝማሪ ፤
ውብ - አፍቃሪ ! - አባራሪ ።

አታንቃሩት ፤
ላታውቁበት ፤
እሱ - ሌላ ፤
ሥራው - ሌላ . . .
" ኢፍታህ ! " - በሉት ፤ . . . በጥሱለት ቀያዳውን ፤
ሑር - ! በሉት . . . . ልቀቁለት ሰናክሉን ፤
ይሩጥ ! ተዉት . . . . እባካችሁ ፤
ይውጣ ! ተዉት . . . . ከቅጥራችሁ ።

. . . ከዕድሩ ደንብ . . . ወጣ ብሎ . . . ከአጋም - ቆንጥር . . .
ተማምሎ ፤
"አለ" ስንል . . .ተፈትልኮ - ባዚም ጋልቦ . . . እኛን ጥሎ ፤
ረስተነው - ስንጋደም . . . ተመልሶ ፤ተቀላቅሎ ፤
. . . አብሮን ኖሮ . . .ያልታዬንን . . . የጉድ ጣጣ ፤
በሮ አባሮ
መርዶም ይሁን ፤ የምሥራች . . . ለኛ ያምጣ ።
አትነካኩት - እባካችሁ
ወዝ የለውም - ከደማችሁ ።

. . . እሱ - ሌላ ! - . . .ብኩን ኬላ ፤
ሥራው - ሌላ . . . . . . .ጉም አዘላ ፤

ውብት — ዘሪ ፤
ውብ - አዝማሪ ፤
ውብት - ወዳጅ ፤
ውብ- አሳዳጅ ።

ቤተሰቡን ፣ - ባልንጀሩን . . . ውሽሚትን - ችላ ብሎ ፣
ቅጠል ሳሩን ፣- ጭሳጭሱን . . . ግብሩን ከፍሎ ፣
በቃምቡራ - ተለማምኖ . . . ሲአል ወርዶ ገብቶ ወጥቶ ፣
ደመነፍሱ-ተግ- ! እንድትል . . . ከኑባሪያት እኩል ተግቶ ፣

. . . ጭራ ቀርን :-ሚሊም ግልጠት ፣ ተፈናጦ ፣ ሰዶ-አሳዶ ፣
ሲቆናጠጥ :- ክብሯን ከብሮ . . . እብዱን አብዶ ፣

. . . "ቦግ - እልሙ" - ናት ፈገግታው . . . ዛር ሲያቃጣው በዋ
ገምቱ ፣
እስከዚያው ግን አታሻክሩት . . . ያሻው ይሁን አትንኩቱ ።

እሱ - ሌላ ! . . .
ሥራው - ሌላ ፣

"ቦግ - እልሚት "- ስትናፍቀው . . . ወዲያ ወዲህ ሲንቆራ
ጠጥ ፣

ተኮርኩሮ ያልሣቀ እንደሁ . . . ለጥሪያችሁ ጀሮ ባይሰጥ . . .
. . . ወዶም አይደል ! . . . የማታምኑ ፣
ዛሬ እመኑ ፣

. . . የርሱን ትቶ . . . "እርሱን ፈርሶ" . . . የኛን ሕንፃ ለመሥራቱ፣
ዛር ተጭኖት . . . መፍገምገሙ . . . ማቃሰቱ ፣

. . . በምናብ ኃይል ፣ ተወጥሮ - ተፍረጥርጦ . . . መጨበጡ ፣
አሊት ድንጋይ ፣ . . . ለማዕዘን ለመፍለጡ ፣
ጉም ለማዘል ፣
ጉም - እንዲመስል ፣ . . .
ተርታነቱን . . . ነው ማምከኑ ፣
አታምኑ እንደሁ ዛሬ እመኑ ።

ተውት በቃ ! " ብቻን ያንጥስ " . . . አትገድቡት ይንቆራጠጥ፣
አቴቴውን-ይማጠናት ፣ ከዱር ይግባ . . . ራሱን ያምጥ ።

. . . . ላታውቁበት :-

አታንቁሩት ፣

ማን አውቆበት ?

. . . እሱ - ሌላ ! . . . ብኩን ኬላ ፣
ሥራው - ሌላ ! . . . ጉም አዘላ ፣

ውበት - ዘሪ ፣
ውብ - አዝማሪ ፣
ውበት - ወዳጅ ፣
ውብ - አሳዳጅ ።

ሰኔ 1982

ላንዳፍታ

የማቅ የሁካታው - ካካታ ፣
የደስታው ጊዜ - ግርግርታ ፣
የእንካ - በንካዋ - ፈገግታ ፣
ጀምበር እስክትጠልቅ- አምሽታ ፣
ሲደነጋግዝ መጥፋቷ ፤

የእንካ - በእንካ ዕድር - አዋዋሉ ፣
ለግዳይ ፡- ግዳይ ጥሎ - መዳለሉ ፣
ከባሕርይ ባሕሪ ተቃድቶ ፣
ከየውሎው ውሎ ተማሽቶ ፣
ምልኪ ፡- ያልመሰለ ለታ ፣
በለስ ፡- ያልቀና ለታ ፣
ለወዲያው መንሸራተቱ ፣
ምሕላስ መላላቱ ፤

የሆነለቱን ፦ ወይ የመሰለለቱን ፦ ለእሽሩሩ ፥
ሲዳዳን ፦ ከጀርባችን ተሸክመን ማሳደሩ ፥
ስንጋበዝ ፦ በአንቀልባችን ለማዘሉ ፥
"ወፍ ዘራሽ አመል -" እንዲሉ ፥
እንደበታችን . . . ጠብ - እርግፍ ፥
ከወገባችን . . . እጠፍጠፍ ፥

በክናዳችን . . .ያገዘ .ደገፍ ፥
ስናደርግ ፥
ስናደራርግ ፤
ሲያዘነብልሳ ሲደፋ - አልቆ የመሆን ገደብ ፥
እህል ውሃ ሲሟጠጥ ፦ ሲደፈን ሁነኛው ጥበብ ፥
የሆነበቱ ፦
ወይ ፦ ድርጊት ለመሰለበቱ ፥

. . . ቆይ . . .!ማለዳህ ቅርብ ነው ፥
ፀሐይህ ይወጣል ሳንለው ፥
የተስፋ ሽንቁር - ሳናሳየው ፥
ቅንጣት ፋታ - ሳንሰጠው ፥
ሕመሙን - ሳናስታምመው ፥

ከመንኮራኩራችን ስንጥለው ፥
ሕሊናችንን ሳይከብደው ፥
ከአፍታው ፥
ወዲያው - ለወዲያው ፥
ለምን ?
ይሆን !
ማለቱ ፦
አይመጣልንም ነበር በሰዓቱ ።

4 - 1 - 81

ወሬ ቆመች

ክፍል አንድ

ሽምብራው ፈሰሰ !

እንደማልነሣ ተጥዬ ... እንደማልጠገን ብወድቅ ፤
እንደማልቀናም አዝምሜ ... እንደማልሠራም ... ባልደቅቅ
እንዳላንቀላፋ ስነቃ ... እንዳልቅመደመድ መቆሜ ፤
ድል በራስ ላይማ ! ያሰኘኝ ...

የእነኝታዎቼ - ሕብር ነው አቅሜ ።

ያሰርኩት ፦ እስሬን ሲፈታኝ ፤
ስካካድ - ከየአጋጣሚው እንጉቻ ፤

ለነፍሴ ጥሪ "ወይ" ብዬ
ማሰቤን ስተው - በጡንቻ ።

ከሐዘን ሐሴት ብቆፍር ... እኔን ስለኔው አስታምሜ ፤
ጥልማሞት ለብሶም ቢፈካ ... ያለ ነዋይ ቢከብር ቅስሜ ፤

... እንደማይርድ ... ተንቀጥቅጨ ፤
እንደማይዘፍቁት ነክረውኝ ... ከቶም ሳልጠፋ ሰምጬ ፤

እንዳይዳልጡት ዳልጬ ... ሲቅመደመዱት መቆሜ ፤
ውስጤም ውጬም ሳይሸነግል ... ከራስ ማበር ነው አቅሜ ፤

ሽምብራው - ፈሰሰ !
ሽምብራው - ፈሰሰ !
የሽምብራ - አፈሳ !
የሽምብራ - አፈሳ !
ወሬ ቆማ ታንሣ !
ወሬ ቆማ ታንሣ !

4 - 4 - 82

ላትሰወር ጠፍታ

ተጠፋፍተን . . . ከርመን ተጠፋፍተን ፣
ተጠፋፍተን . . . ቢሆነን አያል ቀን ፣

ሞፈር ቀንበሬን ሰቅዬ . . . አፈርን ለባለ አፈሩ ትቼ ፣
ማቄን ጨርቄን ጠቅልዬ . . . ጉልባን ጉልበቴን አጥንቼ ፣

ውሎ ዋልኩኝ
በእነኝታዎቼ ፍለጋ ላይ . . . አሰሳ
ኮተት ድርብርቡን ፣
ስቆፍር ዝግንትሉን . . . ስገልጥ ስጥል ሳነሣ ፣

እነሆአቸው ! . . . እዚህም እዚያ ፣
የባተሌ ቤት - ሙያ !

የጓዳው ሸንጎ ተቀምጦ . . . ሸንጐኛው ሲሞላ ድፍድፉ ፣
የወናፉ - ለመጣፍ
የመጣፉ - ለወናፍ
ተጠላልፈው ።-

በአሰሳው ፍጻሜ ትናንት . . . በነች አይደለችም ዳርቻ ፣
የእነኝታዎቼን ብርቅዬ . . . የዘላለሜም መካቻ ፣
አገኘኋት ።—

ዳበስ ፣ ደበስበስ - አረኳት . . . እንትፍ ፣ እንትፍትፍ አልኩባት
ተስፋ ጠበል ረጨኋት . . . አወዛኋት ፣ አረጠብኳት ፣

ነፍስ - ዘራች ፣
ብርሃን ይሁን ! . . .ብርሃን አየች ።

ይኸውና - ላትንፏቀቅ ፣ ዳዴ ቆመች - ዳዴ ሥራ ፣
የኋላ እሸት - የማታ ራት ፣ ልታፈራ ።

ወፌ ቆመች !
ወፌ ቆመች ! ተሽቆመቆመች ።

4-4-82

ግርሻዬ

አፌን - የሆድ አሽከር አድርጌው ፣
ካላመጥክ - ምን አንሶህ ? ብየው ፣
ጥርሴን - የሆድ ባሪያ ሹሜው ፣
የሰጡህን - ገርድፍ ብዬው ፣
ሆዴም - በጐተራነቱ እንዲተጋ ፣
ዝንተ - ዓለሙን - እያዛጋ ፣
ብዕሬም - ያለ ሰላምታ . . . የዕድር መላክት ፣

ዱብዳቤ ዓይነት ፣

ከዚያ ወዲያ . . . እልፍ ላይል ቆርጨበት ፤
ነበር ።

ሕይወት ፡- እሳት ፣ ሕይወት አመድ ፣
ሕይወት ፡- ቀንበር ፣ ሕይወት ወጥመድ ፣
እሳቱንም ፣
አመዱንም ፣
አላየሁም !

ታልሰማሁም !
በቀንበሩ - በወጥመዱ . . . አላጠመድኩ ፤
በእጄ ያለ - በእጁ የለሁ . . . አልተጠመድኩ ፤
ማለት ጀባ - በይ ልመጂ . . . ሕሊናዬ እሽሩሩ . . .
አትለፊ !- አትድረሺ !- ከድንበሩ ፤
ደሞም ደሞ - አዙሪቱን ማስኖ ዞሮ ፣- ለማይዘልቀው ፤
"እንዳች እውነት - እንዳይነግረኝ" አእምሮዬን ደላልየው ፤
ነበር ።

እናማ ፣-

ከአንገት በላይ . . . እስከ ጠጉሬ ፤
ከአንገት በታች . . . እስከ ጥፍሬ ፤
ሆነውልኝ - በጣም እኩል ! . . . እኩል ሥጋ !
አንዱ በሌላው ሳይሠጋ
ነበር አከራረሜ . . . በመኖር ተብዬው ትክሻ ፤
ኮርኩሮ ባያሻክረኝ ፤ . . . ባያደፈርስብኝ ግርሻ ።

ከዚያማ - ግርሻዬ
የሰው አቅሜ ባነተበው . . . ባልተጣፈው ቀዳዳዬ ፤
ገበናዬን በጨረሩ ፣-አሾልኮ ውግ ቢወጋ ፤
እኩል አካሌ ተቃርኖ - በድን ስላሜ ተናጋ ።

በተወጋ ው - ተቦርቡሮ ፤
በድንጋጼው - ተደናብሮ ፤
የበድን ስላሜ ጸጥታ ፤
ጥሎኝ የበነነ ለታ ፤

ፍሬ ሰውነት ምኞቴ - እንደ ወረርሽኝ አየለ ፤
ይህን - ይህን - ሁን እያለ ፤
ያመለጠህን - ያዝ እያለ ፤
ደሞ ነገም - ሌላ አለ እያለ ፤
እንግዲህ - ሰው ሆኘ ላስብ ነው
ማለት ነው ፤
በተቃርኖው ፤
ልክ እንደ ሰው ።

16 - 3 - 81

መላ

የሚወዱትን እንዳጡ ፡- በልቅሶ ቢስረቀረቁ ፣

አመድ - ነስንሰው ፣
ማቅ - ለብሰው ፣
ደረት ገልጠው - ቢደቁ ፣

ከእህል ከውሃ ታቅበው ፣
ወይ ሱባኤ ገብተው ፣
በቁጣት -
ቢብከነከኑት ፣
በእንባ ባሕር ቢነከሩ ፣
ዋይታ ቢያንጐራጉሩ ፤
ዕድሜ እንደሁ - ትንሣኤ የለው ፣
ከአለፈ - ያው አለፈ ነው ።
ይልቅ ጀምበር ሳትጠልቅ . . . ሠላ መምታት ነው መላ ፣
የለዛ እርሾ ሳይሟጠጥ . . . ትክሻ ሳይጐብጥ - ወኔ ሳይላላ ።
በተረፈ ፡- ይኸን በዚያ ሞልቸው ፣
፡- ያንን በዚያኛው አቅንቸው ፣
ማለትን ማን ከተረት ለይቶት ፣
በድርጊት ካልለወጡት ።

እንዲያው - ግን ፡-

የተመኙትን ሳይጨብጡ . . . . የያዙትንም ትቶ ፣
አንጉልም ልብ ሰቅሎ . . . . ከየድባቡ ተጣልቶ ፣
በተስፋ በእቅድ ቁዝምዝም . . . . ይሸነፍ ይመስል - ኑሮ ፣
ሁሌ - ቆይ ! - ሲሉ . . . .

ቆይ ብቻ ! - ገደብ የሌለው ቀጠሮ ፤

የማይጠበቀውን ሲጠብቁ . . .

ነገ ነገን ይወልዳል ፣
ዕድሜውም ይገባደዳል ፣
ወኔውም - ይጨማደዳል ።

ስለዚህ ፦ መላ መምታት ነው - መላ ፣

- ጀምበር ሳትጠልቅ ፣
- ዐይን ጉም ሳይለብስ ፣

. . . ወኔ ሳይላላ ።

መላ - መምታት ነው መላ !

መላ - መምታት ነው መላ !

20 - 11 - 77

ስማ ! . . . ዓለሜ

- "አበባ !" ብለህ ስጠራኝ . . . ለቶሎው አለመባነኔ ፣
ገና ካራስ ቤት ሳትወጣ . . . ትቼህ በየፊልሚያው መባከኔ ፣
ተረት ተጫውተህ ሳጠግብ . . . ገና እንደበትህ ሳይተባ ፣
የጦር አወራወሩን - የሰይፍ አሰናዘርን ፣

ማውራቱ ነጋ ጠባ ፣

ወድጄም አይደል - ዓለሜ !
ጠንቶብኝ እንጂ - ሕመሜ ።

ልጅነትህ እየራበኝ . . . የአባት ወጉን የነሣሁህ ፣
በሣቅህ መጽናናት ስሻ . . . ምላሽ ፈገግታ የነፈኩህ ፣
ለሣቅ ፋታ - እንኳን ሳገኝ ፣
ሣቁ ላፍታ - ያልቆየልኝ ፤

. . . እረ ስንቱ . . . ዓለሜ !
ብርቱ ሆኖ ነው ሕመሜ ።

የጠፋች ሕልሜን ፍቅ ለማየት . . . በሞት ጥላ ሥር ማለፌ ፣
ከስንቱ የጦር ሜዳ . . . እያል ባረሞት ሥሰል ማቶረፌ

ለእናት ዓለም ኢትዮጵያ . . . መቀኪያ ለሌላት ለእንደኔ ፣
የጀግኖቹ ደም አጥንት . . . በየጥሻው መዘራቱ ፣

ወኔዬን ባያንበረክከኝ . . . . ቋንቋዬን ለውጦታል ፣
ታጠቅ ! . . . ብቻ ሆኖ ቀርቷል ፣
መዩ ! . . . ብቻ ሆኖ ቀርቷል ፣
በቀረርቶ ዓይነት - ተገርቷል ።

. . . እንጂ - ዓለሜ
እንዲህ ቢሆን እንጂ ሕመሜ ፣

አላስችል ብሎኝ እንጂ ማለፍ ፣
ሳልጠርግ የናት ዓለምን ጉድፍ ፣

መች አጣሁበት ነበር !
ለኔና ላንተ ጉሮሮ ማደር ፣

. . . ቢጠፋኝ . . . ቤት ማሞቀሪያ ፣
ቤቴ ነው . . . ቋረ ገደል ከዱሩ ፣

እርፍ መያዙ . . . ቢሳነኝ ፣
ጅማሬ ማጥመዱ . . . እያቅተኝ ፣

የናቴም ሙያ . . . ያበላል ፣
ኑሮ መቸርቸር . . . ምን ያገዳል !

ማና ዓለሜ ! እናት ዓለም የምላት ፣
የደማ እናቴ ቀርጠኝ ፣

የፍቅርህ ባውንት እቤ ናት ፣
እናት ዓለም ፤ ኢትዮጵያ ናት ።

[illegible]

እቱ - ልክ ናት ወይ ?

እግሬን በግሬ ላይ - አነባብሬ ፤
ዐረፍ . . . እንዳልኩኝ - ከሳሎን ወንበሬ ፣
ከኀዳም . . . ቡና ስጠብቅ ፣
ሐሳብ ላይ ነበርኩ . . . ሐሳብ መጥምቅ ።

" . . . ዘመኑ ትቶህ ዘመመ !
ምጥቀቱ ከጊዜህ ቀደመ !
ከዘመን ኋላ ቀርተሃል ፣
እና . . . ብታስብበት ይሻላል . . . "

. . . በስንጣሪ - ድምፅ ተወጋሁ ፣
ባንድ - ሣቅ ፍንዳታ - ግራ ተጋባሁ ፤

ሣቅ ለኔ . . . እንደ ትዝታ ነው ? . . . ትዝ - የሚለኝ ፤
ሊይህ ይሆን - መደንገጤ ?

ልቤን - በልቤ ጠየኩኝ ።

. . . ምን ያሥቅሻል - እቱ !? . . . እኮ ምን ተገኝቶ ?
የማንኛችን - ምንነት ፤
ነው :- ከሚዳ የሚሣቅበት . . .?

. . . ምን ዓይነት ሞኝነት ሠርቶ ?

ስዚያውም . . . ሞኝነትም - ብልሃት ፣
ጤንነትም - እብደት ፣
እብደትም - ጤንነት ፣
መሆኑ - አለመሆኑ ፣

ውል ቢኖረው እንኳን - መቀመሪያ መጠኑ ፣
ቀመሩን ይዘሽ . . . . ከሣቅ በላይ ብትሥቂብኝ ፣
ይኸን ያህል - ባልነደደኝ ፣
ይልቅ . . .

አቋረጠችኝና :-
በሣቅ ፈነዳች እንደገና ፣

"እ.ሽ ! . . . ምንስ ፡- ሲማር ይመለሳል ፤
እንበል ፤ . . . ተመልሶ ግን ይሞኛል ፤

እብደት !
ጤንነት ! . . . ይኸንም ከዚያ ይበልከው !?
ሜፍ ሜፋን ይዘሃል . . . ይኸ ስም የማይሰጠው ፤
ጭራሽ - ለለየለት ነው ፤

እብድ አትናቅ - ጌታው ! . . . እብድነቱ ካልተሰማው ፤
ለውጪው ዓለም ነጸብራቅ . . . እሱነቱን ከገደለው ፤
ጤናስ ቢሆን ከዚህ ይበልጥ - ምን ሲያተርፈው ፤
ከሰላም አንጻር ነው ፡- ትንታኔው ።

ማቅ በማቅ - እየደበለች ፤
አሁንም ትሥቃለች ፤

" አንተ ግን ካገር ዘመን ኋላ - ተጎትተህ ፤
የግል ዓለምህን - ፈጥረህ ፤

ራስክን ብቻ ያቀፍክበት - ክንድህ ሲዝል ፤
ዘመኑ ትቶህ ሲዘም - ለብቻህ ቀና ብትል
ጤንነትህ ጤና ሊባል . . .?

. . . ይኸን ያለማወቅ - እብደት ያልሆነ ሕመም ነው ፤
እንዲያውም ይግረምህና . . . ከዲዳውና ከደንቆሮው ፤
ከመሃይሙ ባለደዌ ጎስቋላው ፤
ምን ልበልህ -?

ከጉንድሹ - ከቁንጥሹ - ከጠማማው
ከይች ምድር ዝቃጭ ምሳሌው ፤
ዐወቀው መቅረትህን - ወደ ኋላ ፤
አይደለም ንግግሬ - የተማላ . . . "

በልቤ ምርር ብዬ - ረገምኳት ፤
ያረቅ ማቅ . . . ያውም ማቅ ለረሳች ሕይወት ፤

ትሥቃለች ፤
ታስካካለች ፤

አካሌ ሁሉ . . . ዐይን ሆኖ አየት ፤
ግራ ተጋብቻለሁ . . . የምን ታምር መላክተኛ ናት ?
ብዬ . . . ትግሥቱን ጨልጬ - በትንፋሽ ፤

" በወግ እንደሚቀመሱት - ተረት ፣
ሚዛኑ ቅርብ አይደለም . . . የመቅደምና የመቅረት ፣
ጉስቁልናም ሆነ ሕመም ፣
ለመቅደምና ለመቅረት - ምልክትም አይደለም ፣

. . . እቴ ባትሥቂብኝ - ደስ ይለኛል ፣
መናቅ አልወድም - ያመኛል ፣
- ይበቃኛል ፣

አትሣቂብኝ - ይመረኛል ። . . .

ቃጭል ድምፅ . . . ኪል ! ኪል . . . ኪል ! ኪል !

ደረቅ ሣቅ . . . ኪ ! ኪ . . . ኪ ! ኪ !

ምን ላኩብኝ እምላኬ !? . . .

ሰላም ለኪ ! ሰላም ለኪ !

የሰይጣን ማርያም

እንዘ ንሰግድ ለኪ !

ሰላም ለኪ ! ሰላም ለኪ !

የሰይጣን ማርያም . . .

. . . አሁን ይኼን ምን ልበለው ?
ሕይወት . . . ሰውን ታጠምደው !
ወይስ . . . ሰው ሕይወትን ያጠምዳት !
የታመነም -! ያልታመነም -! . . . ወግ አርገን ስንቆጥራት ፣

ዓማውን - ወይም ዓማ አጥማጁን ፣
መሆናችን - ወይም መምሰላችን ሳይለይልን . . .

ብቻ :- የሰው እሱነቱ . . . እናር ናት ፣
ጥንግ :- . . . ገና ' ሚሔወቱበት . . .
. . . እንያዩ ወዲያ !

(ከወዲህ)
ከወዲያ ያለው - ቅልም !

እንዴዬ - ወዲህ ፦
ከወዲያ ያለው - እልም . . .

ም . ስ . ኪ . ን . . .

. . . ግድ የለም ! . . . ልተወው ፤
እኔም - አልጨርሰው . . ."

እንዴ -! ' ውነት ሆኖስ ቢገኝ !
ጉድፍ በገመና . . . እንከን በጓዳዬ ቢኖርስ ያልታዩኝ
እያልሁ : . . . ልጅነቴን ቃኘሁ ፤
ጉልምስናዬንም . . . ሁላ ሁሉን አየሁ ፤
ኑሮዬን ሁሉ አውጣጣሁ
ለድርድር ። . . .

. . . የማለዳ ጎህ - ተስፋን ፤
የሠመረ ትዳር - ጸጋን ፤

የአፍላን እንቅልፍ - ጸጥታ ፤
የሰላምን አየር - እፎይታ
ዐውቃለሁ !

እንዴት ዘመን አመለጠህ - እባላለሁ ?

. . . የሐሜትን - ክኩሶ መምረር
የሐዘንን - ጥላ ከምር ፤
እጅ - ' ግር - የሌለው ውሸት ፤
እንደ ጢፍ - እሚነድ ቅናት ፤
ዐውቃለሁ !

እንዴት ዘመን ረገጠህ - እባላለሁ ?
. . . ወጣትነት ፦ ትንሽ ዓለም . . . እንደ ጥላ ፤
ሳይታወቅ ፦ እ.ል . . ፍ ፤ ሲል . . . ሲፈረካከስ እንደ ሸክላ ፤
ለዛ - መዓዛ ፦ ከድሜ አበባ ጋር . . . ሲረግፍ ፤
ባሕሪይም ፦ ሲለዋወጥ . . . ክንፍ አውጥቶ ሲከንፍ ፤
ዐውቃለሁ !
እንዴት ዘመን የገፋህ - እባላለሁ ?

... ድንቁርና ገላን :- እቅፍ ማድረግ ፣
መሆን :- የጐበዝ ምኞትና ወግ ፣
የሳቅ ስሜት - ካባ ተላብሶ ፣
ማለፉ - የጊዜ ሐቅ መሆኑ ፣

የአፍላነት ወራት እሸት ተቃምሶ ፣

በመቃብሁ !

እንዴት ዘመን ረገጠህ - እባላለሁ ?

... የከበሉ ልጅ ነገሬ :- የነረደዋ ትራስ
ከፍቅር ዐይን በመነጨ :- የስሜት እንባ ሲፈስ ፣
በነገር ጥያቄ - ዒላማ ፣
ለጋ ፍቅር ስትቀበል - ስትሄማ ፣

በመቃብሁ !

እንዴት ዘመን አመለጠህ - እባላለሁ !

... የሙዚቃ ቅኝት ቃና ፣
ስብር ወለጋዴ መንፈስ ሲያቀና ፣
ፊልጥና ዘያብ ፣ ... የተቀባበ ቅኔ - ልብን በሉስት ሲሞላ ፣
ነፍስ ስትረካ - ከትምህርት ፣ ስትፈካ እንደ ማብላ

በመቃብሁ !

ለማውቀውም ሐቅ እገዛለሁ ፣
እንዴት ከዘመን ኋላ ቀረህ - እባላለሁ !

" ... ኢ.ዮ.ጵ. ስም ነው " የምልህ ፣
ርቃኑን የቆመ ሐቅ ምን ሊጠቅምህ !
የዚህ ዓለም ዘቀጣ - ምንስሌው ፣
ቅያም ያልነው ፣ ዲዲመኝ ያንቆርጠው ፣
ለዕለት ጉርሱ ፣
ጋፍረሳን መጋረጃ ለለብሶ ፣
ሲያሰለስል - በመንካ በሕልሙ ፣

በረንዳ ሌሊት ተጋድሞ ፣ ከከብ ሲቆጥር ፣
ሲያምር ከለመመ

ነገን ፡- እንዴት እንደሚያልፍ - ያስብ እንደሆን ፣
ልብ - ብለህ አይልኝ ! . . . ከዘመኑ እኩል መሔዱን ፤

. . . ከባዕታ በፊት በልደታ ጀምሮ ፣
አቦን አማሎ ሥላሴን ዞሮ ፣
ከሊቀ መላክ ፡- ሚካኤል ደርሶ ፣
ለገብርኤል ትንሽ አዚሞ . . . አሞካሽቶ
ለቀን ማርያም ከደረሰ . . . ጊዮርጊስን ዶጅ ጠንቶ ፣

እንዲያ 'ንዲያ - እያለ . . . ሐየ ዘጠኝ ይደርሳል ፣
" ስለ ባለ እግዚያሔር ! . . . " ማለቱ፡

ስሙ ለሽምደዳ ይቀለዋል ፣

ጻድቁን - ያመጻድቃል ፣
ስለ ኃጥኡ - ይማፀናል . . . ባይሆንም ያስመስለዋል ።

አየህ -! ?
ተረዳህ - !

የ'ማልክትን ዘር መቁጠር . . . ሐረግ መሳብ ተስኖት ፣
ዝም ቢል ኖርስ -? በቃ ! አክትመለት ፣
እንጀቱን ባንጀቱ አንቆ . . . ሆዱን በሆዱ ውጦት ።
ከጊዜ ጋር መሔድ ይሷል ፣
ከይህ - ከይህ ይጀምራል ።

" . . . የሕይወት ውበት ጤዛ . . . ያለ ዐሐይ የሚረግፈው ፣
አብሮ በመንፈስ ፈንታ . . . . ቆሞ በነፋስ ሲመታ ነው ፤"
ያለው - ማነው ?
ይኸ .ይኸ ነው ፡- መንደርደሪየው ፣
በሰያፍ - መመሳሰያው ።

ካልሆነም ፡- መምሰል ነው . . . ሙልጭ ብሎ ፣
ሕሊና ፡- ብሎ ነገርን ጥሎ ፤

" . . . ሕሊና ፡- ከየዋሆች ልቅሶ ዜማ የወረስናት
አንጉል ቢጤ ዘፈን ናት . . . "

ያለስ . . . ማነው ! ?

አጋጣሚን - ሲረማመዱ . . .እንዳጋጣሚው ግንባር ነው ፤
እና - ምን ቸገረህ ? . . .
ትዕቢተኛ - ያጋጠመህለት ፤
ክብረ ዳረጎት - ቁረጥለት ፤

ድንጋይ ወርዋሪው . . . ሊወረውር ሲል ፤
ወንጭፍ ሠርቶ ማቀበል
ሽንጡን ሲዳብስ . . . ሲፈልግ - ጩቤ መሳይ ስለት ፤
ካፍታው . . . ጣምራ ጦር መስጠት ፤
ድንቅ ! ! . . .ብሎ ካወደሰማ ፤
በጣም ጥሩ ! . . .ድገመው አንተ በዜማ ፤
መኮነን - የፈለገለት ፤
አንተው - ሲኦል ሁንለት ፤
በጽድቅ - የሳተ እንደሁ ፤
መቸስ ምን ይደረግ ? . . .መሳሳት ነው ፤
አትበል :- ተሰለቻችሁ ፤

በተረፈ ሲረግም :- መርገም . . . ሲያወግዝ ማውገዝ ፤
አለየማ መቅረትህ ነው . . . ከንቃቃታም እግር ተረከዝ ፤

ንቃቃት . . . ታውቃለህ ?

የእግር ንቃቃት አይተሃል ?
አፈር ፤ አሸዋ ፤ ጠጠር ፤
ትንንሽ ኮረት - ይውጣል ፤
ልብ - ያለው . . . ልብ ያረገዋል ።

ብላ . . .ቀጭ ቅው ! እያለች ፤

እንዲህ . . .!ወደ ኋላ ! . . .ጠጉሯን እየመታች ፤
ወደኔ - ቀረበች ፤

" ማብራሪያ . . . ! ሽረ ጥያቄ አለኝ !
እስተ ድንግርግሬ - አትተይኝ !
ከእምነቴ - ወይ ከእምነትሽ ሳታደርጊኝ !
ከሐቆቹ - አጣልተሽኝ !

" . . .ሽረ ትንሽ . . . ታገሽ ፤
ጠይቂ - ልረዳሽ "

እጆቹን አጣምሮ . . . ቁጭ ቀው . . . እያለች
ፍቅሯንን · ዉጤመረች
ልታንቀኝ መሰለኝ . . .

በማመኑ · ተጠጋች ፤

ከጓዳም . . . በቢያሬ ፣
ሙኝች . . . . በመማረር ፣

“ጋሼ ! ጃሬ ጋሼ . . . ! !
ጠማው · እንጀ ምነው ፣
በረያብህ = በኋው ፣
ስቃዩ ላነማ . . . ፍንጃሉን ልውሰደው ?

እቱ፤ አፈገፈገች . . . ጠፋም ሰመመኔ ፣
ራቤን · ባገኘው . . . እዚያው ከሳሉኝ ።

18 - 1 - 77

አንዳንድ ጊዜ

እንደማይ ዘነብ አመጣጥ . . . አንዳንድ ጊዜ ፣
በምሻ መንገድ ከተገኘ ብልጥ . . . አንዳንድ ጊዜ ፣

የማይ በረዶ . . . መጠበና ፣
የብልጥ ምኞት መከረሩ ፣

ምስት የፈጠነች ለት . . . አንዳንድ ጊዜ ፣
ፊሪ በለበ የቀናው ለት . . . አንዳንድ ጊዜ ፣

አቤት . . . ! የቀን ሌሊቱ ማዋለሉ ፣
የፈሪም ቀንበር መወደሉ ።

ጀግና ሽንፈቱን ሲያማ . . . አንዳንድ ጊዜ ፤
እውን ከቅዠት ሲስማማ . . . አንዳንድ ጊዜ ፤

ሽንፈት እጀግና ላይ ከፋቱ ፤
የቅዠት ሲሳይ ማስጠላቱ ።

ደግነቱ
አንዳንድ ጊዜ ብቻ መሆኑ ።

3-12-80

አልሞትም አልልም

አልሞትም !

አልልም

እኔም እሞታለሁ ፤ ከደንብ ውርስ አልወጣ ፤
ካፈር ልብሴ በታች ፤

ሽፋኔ በስብሶ ፤
ከንብንቤ ፈርሶ . . . በቀሌ እስኪወጣ ።

እሞታለሁ እንጂ . . . ለምን እኔ ብቻ
ልታጣ - ከተርታ ፤

ዳግም ትንሣኤዩስ . . . ጽድቅ መከወኛው ፤
የት ብሎ ያገኘኝ !! የቀጠሮ ቦታ ።

አልሞትም !

አልልም ።

እንደ አማሚቱ ነው ፤
እንደ አፈር አልባሱ . . . በቀለም የሚያምር ፤
በዘሪ 'ጅ - ተዘግኖ ፤

ሲበተን - ተረግጦ . . . እንደማይፈለግ - እንደሚጣል ነገር ፤
እንደ ቀባሪው ነው ፣
እንደ ገበሬው ስልት . . . ሞቶም በቀዬ ቶሎ ፤
እስቲ እኔም ልሙተው !
ሞቴ ለምን ይቅር !? . . .ያልሞተ መኝ በቅሎ ።

አልሞትም

አልልም ።

ለከልከሊ

8-11-81

እብድ የበላው በሶ

የልጅ ቤት ፦

የከክ ስጥ - ሆንሽ ፣
ሁሉም ዘገነሽ እቴ ! . . .ሁሉ ዘገነሽ ።

የቡና ቁርስ ፦

አፍ - ማሟሻ
የልጅ ሀዋቂው - የኩል ድርሻ ፣
እንጃ - እቴ ! ምንቺን ነገር መዳረሻ ።

የእንቅብ አስር ፦

የአለሌ - ማላመጃ ፣
የስፌድ ቆሎ ፦

የወጠጤ ራት መፈንጫ ፣

እረ ! ምንቺስ ነገር እንጃ
ሌኔም

ላንቺም - እንጃ !

በተኑኝ ፤
የውያጣ እብት   መንገዱ ...
ነፋስ የረበሹ   ...
አረገኝ ።

ቀለሉኝ ፤
ጉያዎቼ ፤ የመበጋጀ ንብረት ፤
ከሌ የሚያኮተኩት ፤
አረገኝ ።

እንዴም ፤—

ሳትሆኝ - ሆነብኝቸው ፤
ሲበክሉኝ - በክፉኝቸው ።
የቀን ሙያያኼም - ተማሰሱ ፤
ከማትቨኼው - ተኳሰሱ ።

የማይጠኑ - የማይሳቁሉ ፤
ዱካዎቻችኝ - የበጠመው ፤
ወራቶችኝ - የዕዳ ጃዋ የሰሩ - የማያሰሩ ፤
ትዝቶችኝ - በምንናው - ከማንገው ያጸዱ ።
ምስኪንቱ ፤
የባንኮኒያቱ ።

11-11-82

ዝምታ

ልባችን እኛ አመንጭቶ .... ጉርፍ ወርቶ ሲያጎፉ ፤
ወኔያችንን አቁራምዶ ... እንገታችንን ሲያስደፉ ፤
ነፍሳችን - በትካዜዋ ቀዝቅዛ ...

ሰትለብስ ቴቢት ነጠላ ፤

ጓደኞቻችንም ሲመሰክሩ . . .

አርምሞም ጥላሸት ጥላ ፣

. . . ይኸን የሰላማችንን ማዕረ ሞት ፣
ጫኙና የሆነብንን - ብሶት ፣
እንለየው . . . ካልንማ ፣
እንረዳው . . . ካልንማ ፣

ከዚያም - ወዲያ
ከዚያም - ወዲያ - ወዲያ . . .
የስርየታችን ቀን - ምጽአቱ ፣
የቁርጥ ግልግላችን - የሽረቱ ፣
የንጋት ኮከባችን - ምልክቱ . . .

እንደ መብረቅ . . . ወገግታ ፣
እንደ ሕፃን . . . ፈገግታ
ይለይልን - ካልንማ ፣
እንረዳው - ካልንማ ፣
እንታገሥ . . . !
የሚሻለው -
ቆይታው ነው ፤

በዝምታ ቋት - ተሰብጦ ፣
እንዳንጠብቅ - በከንቱ ፤
የበይን ቃላችን - ብልጠት በልጦ ።

አዎ . . . . . .
ዝምታ ነው- የቃል ውሉ ፣
ዝም ! ብያለሁና - ዝም በሉ ፣
ለምን ዝም አለም - አትበሉ ፣
ዝምታ ነው - የቃል ውሉ ።

ነፍሳችን በትካዜዋ ቀዝቅዛ . . . ስደርብ ቴቢት ነጠላ ፣
አመሳክሮላታል ፊታችን . . . ብናረም ጥላሸት ጥላ ፣
ገበናችን ጉልቶ ተዋፎ ታይቷል ፣

በግንባራችን አሻራ ፣

ግንባራችን አሳቶታል ፣

የነፍስ አካሌን ውበት ቢራ ፤

ስለቃቁጣቸው ወዲያ ፣
ያን አስኪፈርርልን ተናዴ . . .

እንደእሱ — ዝም ይሻላል ፣
ዝም'ኮ ነው — የቃል ውሉ ፣
ዝም ! ብዬላቸው — ዝም በሉ ፣
ለምን ዝም አለም — አትበሉ ፣

ብትሉም ፤
አይገባኝም ፤
ውነቴን ነው ! አይገባኝም ።

30-2-82

“ይሙት በቃ” በሉት

እሱ — ለሱነቱ ባይተዋር ከሆነ ፣
የራሱ ካልሆነ ፣

እይታው ካልበራ የኛላማው ዘል ሆኖ ፣
ተበፍቶ ካልሰለነ ፣

እየኖረ ሞትን “አሽ” ካለ ተልሎ
ለሽንፈት ካደረ ፣

መላቢስ ከሆነ ፣ መላው ከተጠነ ፣
መላው ከተበሪ ፣

ለምንም ፣ ለምንም ፣ ለምንም ካልበቃ ፣
“ይሙት በቃ !” በሉት ፣ በቃው ይሙት በቃ !
በቃ ይሙት በቃ !

17-5-78

ዱባና ንፍሮ

ቶሎ ሙሉ ዱባ . . . ታሽቆ ፤
የዱባ ቁርጥ . . . ተንፈቅፍቆ ፤
እንቅብ ስፍር . . . ንፍሮ ፤
ኩስኩስቱን ሙሉ . . . ተነፍሮ ፤
እሳቱ ላይ . . . በእንክርት ፤
ዛሬም አለ ፤- ከመደቤ ፊት ለፊት ።

ሁሌም - በየቀኑ ፤
ባየው ባየው - እሱኑ ፤
ቶሎውም -
ኩስኩስቱም -
እንክርቱም -።

እቀምሰው ብል - ከምጥኑ ፤
እበላ ብል - ከክሸኑ !
ዛሬስ አልጥምህ አለኝ . . . ሌማቱ ፤
ዱባ ከንፍሮ - ብልቱ ።

እንዳልበላው . . . መታከቴ ፤
ድንገቱ ዛሬ - . . . ኩራቴ ፤
እንዳልተወው . . . ፍራቴ ፤
እየታየኝ የራብ ሞቴ ።
እዬ . ሆድ . . . ! !

-ጊዜ ቋቱ . . . ከርሞን - ከርሞ ፤
በ"ቀን አለ " . . . ከዳን ህድሞ ፤
እንዳልቆየ . . . መርጎ ችሎ ፤
ውስጡን ከውጭ . . . አቻችሎ ፤
የእርሾው ድፍድፍ . . . በስሎ ፈልቶ ፤
መጣላሊቱን ከነምርጉ . . . ጥሶ ወጥቶ
በቃኝ - ካለ
በቃህ - ! ካለ . . . ካወጀማ ፤
ምን ልሆን ነው ! ? መዘርፈጤ

የማነኝ ልል !
የማን ወላጅ ! . . . የማን አርማ ! !

እንግዲያስ . . .

ቼ -! ፈረስ . . . ቼ ቼ ! !
ኅሱ ! ዱባና ንፍሮም ጌቶቼ !
በልቼ . . . ላብላላችሁ ፤
ጋልቡኝና . . . ሊጋልባችሁ ፤
እንቀማመስ - ደራ
እንሳለል - በየተራ ፤
እንፋተሽ - በያይነቱ ፤
በውስብስብ - አዙሪቱ ።
ቼ ! ፈረስ . . . ቼ. ቼ ! !
ቼ ! ፈረስ . . . ቼ. ቼ ! !
ቼ . ቼ !
ቼ !

ላባቴ ለፀፀቶ ሰለቃ ሰሊ ሃምዛ

ሐምሌ 1980

ጃልዬ አታምሰው

እንዴታ . . . !

መኖር ሥራ ነው . . . ያውም ለእንዳንዱ ያለ ገበሬ ፤
ሥራም የመኖር ሱሪ ፤
ቦታ አትስጥ . . . ለጥርጣሬ ።

በትነህ . . . አበራዬኸው ፤
በርብረህ . . . አመነሸኸው ፤
ለየኸው - ጥሬውን ከገለባ ፤
በል ፡- ገለባውን ከምር . . . ጥሬውም አቁማዳ ይግባ ።

እናም ፡-

ፊት ለፊት ቁም ፣
ቢያሻህ በክምሩ ... ወይንም አቁማዳው ላይ ፣
ያ - ቻትና ፍቅርህ ... እሩቅ የምትታይ ፣
'ባክህ ሥራ አታብዛ ... ዳግም አትቀላቅለው ፣
ሁሉም ያንተ ድካም ... የትናንት አዋዋል ፣
የዛሬ ምርት ነው ።

ጥሬው ፡- ሲቀሰብህ ፣
ለዛሬዎች ስንቅህ ... ፍቅርህን መሳቢያ ፣
ገለባም ፡- እትናቅ ፣
ላምና ከብትነትህ - ይሁን ማደለቢያ ።

ጃልዬ ... እታምሰው !
በቃማ ... ከምረው
ቆጥረው !
እሰረው !
ጃልዬ ... አታምሰው ፣
ያብን ! አርገህ ቋጥረው ፣

ተወጣተህ - እዮት ፣
ፍቅርህ - ያ. ቻትና ... ስታይ ተንደርደረው ።

ጃልዬ - አታንኩረው
ቅደምን - ካሁንህ ... አታደበላልቀው
ጃልዬ - አታምሰው

24-11-82

እማኝ ልቤ

የዚያን ለታ ! . . .

እምላክ በድንገቴ ተመስሎ ፣
በሥጋ ልፈያ አታሎ ፣
በዕቃ. ቃ. ጨዋታችን . . . መሳለቂያው ሊያረገን ሲሻ ፣
የድንገቴ . እፍ . ጥልፍ ፣ . . . የፍቅር ርግብግቢቱ ቅምሻ ፣
ባክናፍ ይዛ ብታከንፈን ፣
መውደድ ፍሟን ብታጭረን ፣
በመሳሟ ብትስመን ፣
በወላፈኗ ብታጥነን ፣
እግዜሩን :- ከነድንገቴ ረሳነው ፣
ማቄ - ስቅ ! -እስከሚለው ።

ከዚያማ - !

ገላሽን በገላዬ ስገምደው ፣
ጸጉርሽን በጣቶቼ በትኘ :- ወደ ጫንቃዬ ስጥለው ፣
የስሜታችን ግለቱ ፣
የመፈላለጋችን ስበቱ ፣
የርካታችን ብዛቱ ።

ያኔ ! -

እንዲህ :- ደረቴ ላይ እንደሟሟሽ ፣
ልቤን ዘልቆ ሲሰማኝ ስስትሽ ፣
"ውነትም ደግ ሳስተሻል ፣
የፍቅር አምላክ ነግሮሻል ፤"
አለሽ - ልቤ ፣
አማኝ - ልቤ ።
ይብላኝ - እንጂ እኔ መቸም ፣
አለሁ - የለሁምም - አልልም ፣
ዕንቡጥ ፍቅርሽን ቀብሬ ፣
ስቀቀኑን - እያለምኩኝ

ምን ይሆን ? እያልኩ ብደሬ ፣

መባነኑን ማን ባኖልኝ እኖራለሁ ፣
ተይው ወዲያ ፡- እኔ መኖሬን ትቻለሁ ።
ይኸውልሽ ፡- መገረምን ተገረሚ ፣
ከ ' ቡይ ልቤ - መርዶ ሰሚ ፤
መቸም ፡- አለ . . .

''መቼም ፡- የኔና - ያንቺ የፍቅር ላብ ፣
ዋግና አንበጣ እንደሚያስነሣ ዝናብ ፣
ለሲሳይ ሳይታደል ፣
ውጦት የትዝብት ደለል ፣
ቅራሪ እንጂ . . ቢሆን እንቃሪ ፣
ለማዕረግ ይበቃል ብለሽ እንዳትጠራጠሪ ።''
አለሽ - ልቤ ፣
አማሽ - ልቤ ።

"ሌላው ይቅር . . .

አንቺ ፡- የዘፈንሽበት ዱሩ ፣
እኔም ፡- የዘመንኩበት ዕድሩ ፣
ኑሮሽ ፡- ያገኖዳኘሽ ዘይቤ ፣
የኔም ፡- ሽፍን ቅምሩ ልቤ ፣
የሚያነሣው ፡- ተረብ ማዕበል ፣
ምን ተደርጎ ቢሸነገል ?
የፍቅር አዝመራችን - ያምራል ፣
ኤዲያ ፡- ተይው ! . . .በዚሁ ቢቀር ይሻላል ''
አለሽ - ልቤ ፣
አማሽ - ልቤ ።

ከማይኮነው ፡- ኹነት ተገኝተሽ ፣
ከማይገኙበት ፡- ባሕር ተጠልፈሽ ፣
ልማደ-አዳሬን ፡- ብትሽሪው ፣
አመሌን ብታለስልሽው ፣
የወግ ሞገድ ፍራቻ ፣
ለመሸሽ የምላስ ዛቻ
የሚያድገውን ገላ ገደልነው ፤

ያቆራኙንን ሰንሰለት በጠሰነው ፣
በሥጋችን ሠጋንበት ፣
ዕጣውን እንዳይቆጥርበት ።
ደህና ሁኝ ደህና !
ደህና መሆን ደህና ።

ግንቦት 1979

ጥሩምባ

እናንተ . . .
እንደ ውቃቢ . . . መንፈስ ፣
እንደ ጻድቃን . . . መቀደስ ፣
በጣኦት ቅኝት . . . በገና ፣
እንደ ታቦት . . . ኀብረ ዜማ ፣
ከሐዘን ከማቅ . . . ተቀምሮ ፣
ከሩ ከደጋ . . . ተመሳጥሮ ፣

ኀብረ ትራማይሌ - ተመጥኖ
ከማልጥጡ . . . ከቀረጡም ተደፋፍኖ ፣

. . . የማንጥል - ቅጥጥል - ተደደብ ፣
የቀረባችሁ ካለ ተረማዘ ፣

እለቱ ‘ውኅት ብያችሁን ውለዱ ፣
ከየልድፍችሁ - ተፋረዱ ፣
እለቱ ሐቃችሁን - እምቡ ።

እናንተም , . . .

ሰማይ - ምድሩ ፣
ለአደባባይ - ተጠሩ ፣
ከዋክብት - ከማብሬታችሁ ደኅጡ ፣

[illegible]
[illegible]
[illegible]

እና . . . .

እና - [illegible]
[illegible] - [illegible]
[illegible] - [illegible]
[illegible] - [illegible]
[illegible] - [illegible] ።

2? - 6 - 82

እርጌ ልጅ

ዕድሜ እንደ 'ድማስ ማዶ ድንበር ፤
ረዥም ረዥም ደርሶ ከመምላቂየው በር ፤
ሊያዩት እኩሉ - በእኩሉ ተደርቶ ፤

፺በቱ ' ፺ሀ መበት ' - እንዳሉቱ ፤
ግና - የዕድሜን ጸጋ ማስገንዘቢያው ፤
ድንገት ቢመጣን ለወዲያው ፤
ለካስ . . .!
ሕሊናው - ውርጭ ተመቷል ፤
ፍሬም እንደ ትናንቱ - ቀርጭጿል ፤
የአምና - የአምናውን - ከርሞ ከርሞ ይደግማል ፤

እርጌ ልጅ ይሏል ፤
በደሁ - በደሁ ይገለግል ።
እርጌ ልጅ !

2 - 6 - 78

ይቅር ?

ፍርሃት ነው . . . ጨለማ ፣

ጨለማስ . . . ?

. . . የፊሪ ሸማ ።

ከጨለማ - እስቲዋዙ ፣
ላለመሰሉብ - ለመዘዙ ፣
ዐይን ፦ በጁ - ይታሻል ፣
እጅም - ዐይንን ያሻል ።

በፍጥረት እስስር ቅማሬ - በሕገ ሽክርክሪቱ

ሲጸና - አይቀሬነቱ ፣

የማይገፋትስ - ጉራ

ተራ ፤

ዙር . ተራ ።

ና . . .

ዮቱን ሲሮጣት ጨለማ . . . ግርማ ጠላቱን ሸሽቶ ፣
ፍረት ያጨናብሳል . . . ብርሃንም ዐይንን ወግቶ ፤

ጠላትነታቸው - የወል ዐመል ድንበራቸው ፣
ዐይንን ማሳሸታቸው ፤
በየተራ - ተራቸው ።

ታድያ "ማኑ" ተቤገር ይባል ? . . . ለማንኛው ጊታስ ይጉብደድ
ለጨለማም ዐይን ታሽቶ . . . ለብርሃንም ሲጨመደድ ።

ሁሉስ - ቢቀር . . .?

ይቅር . . . ! ?

2 - 11 - 82

እንደ ኢዮብ

አሁን ስምንን ደሞ . . . የመጣብኝ ነገር አባዜ ፣
ሳስታምመው ውዬ ማደር . . .በእሽሩሩ ውዝዋዜ ፣
ካልቀረልኝ መፈተን ሁሉን አጥቶ ፣
በናላዬ ገዝፎ ሞልቶ ፣
ምናምኔ መበደኑ - ካልቀረልኝ
አሁን አሁንስ . . . ኢዮብን መሆን አስመኘኝ ።

ማቅ ለብሼ - ሰቆቃ አምባ ፣
እንባ ኩሬ መስነቁ - ነጋ ጠባ ፣
ማቅ ሽርጦ - ከል ደርቦ
አመድ መደብ - ተቆራምዶ
በጎ ትንቢት - ተቀጣጥሮ
ካምላክ ፈቃድ - ተመሳጥሮ
ድሮን - እያሰላሰሉ ፣
ተሐድሶን - እያሰሉ ፤

ከዓለሙ ዱር ፣ ከሰው ጫካ . . . መሆን መናኝ
ዛሬ - ዛሬስ . . . ኢዮብን መሆን አስመኘኝ ።

ቀላል ነው . . . እንባውን ባላጣሁ ነበር ፣
የዐይኔን ቆብ . . . ምንጩን መቆፈር
ማቅም ያደኩበት ነው ፣

ስለ ከል ድብዳብ ልባበስ ፣

እምነት ግን ከየት አባቴ ?

ትንቢት ያለ እምነት አይደርስ ።

8 - 2 - 75

ይብላኝለት

በደረቅ - የሐሩር ወራጅ ጣሪያ ፤
ቆሌ በራቁት - መንደር ዙሪያ ፤
ፍጥረት - መላውን ተኮልኩሏል ፤
ሕይወት ፡- አለሁም . . . የለሁም . . . ይላል ።

ከዚያች መንደር - በላይ ፤
ሲያቅኑ ወደ ላይ - የላይ ላይ - ወደ ላይ ፤
እነሆኝ ፡- ሰማያዊ ፤
ንጭ ሰማያዊ . . . የነጠፈ ሰማይ ፤

የዝናም ምልክት . . . ምናምን ሲፈልግ ፤
ዓይን ቢወረወር . . . ከነፌዙ ሰማይ ጥግ ፤
አንዳችም
አላየም ፡-
እና መልስ ሲያጣ . . . ወደ ታች ከነፈ ፤
ማየት ፡- በማየት ጉድ . . . እልፍ አለፈ ፤
የሞት ጽላል ድርብርብ . . . ከንዳዱ ኅብር ሠርቶ ፤

የአባድር ወገኑ - ድምቀቱን ፤
ቀዬ እድሩን - ወዘናውን ፤

የአገር ለዛውን . . . አሳጥቶ ፤
አንጀት - ካንጀት - ተናንቆ ፤
ምላስ - ከጉሮሮ - ተሰንቆ ፤
ዐይን - እንኳን ከዐይን ርቆ ፤

"ጨረቃ - ድምቡልቡቃ
ዓጄ ቤት ገባች ዐውቃ "

የነማሙሽ - ዝማሬ ተሰርቆ
ተጥመልምሎ - ተደብቆ ፤
የቀን ቅዠቱ ፡- "አለመኖር" ሞትን ቀድሞ
ጣር በሰቀቀን አብጦ . . . አንደበት ግን ተስለምልሞ ፤
ዐይን ታዝቦ . . . የሲኦል ምትሃት ሰፈረ ፤
ማየት ፡- በሚያየው ጉድ ነፈረ . . .

. . . ዝምታም ፡- ለመታዎች ሀይን የገባው ፤
ያን ጊዜ ነው ፤
ነፍሳት ፡- ረጭ - እንዳሉ ዝም ፤
ሁሉም ዝም ፡- እንዳለ ዝም ።

በዚያች - ትንሽ ጉጥ ምድር ዙሪያ ፤
በዚያ - የሐሩር ውሽንፍር ትቢያ ፤
ሞት መላኩ ፡- ሺህ በክንፉ ሺህ ባክናፉ . . . የሚጸራ ፤
ሺህ በጥርሱ ፡- ሺህ በጥፍሩ - የሚያደባይ . . . ሞት ጀጸራ ፤

ይለዋል ! . . . ይጨፈጭፈዋል ፤

ያንን - በለው ፤

ያንን - ያዘው

ይለዋል ! . . . ይባባለዋል ፤

ያደለበውን - ቁርጥ
ያከረመውን - የከረመውን - ዝርጥጥ
ያበሰለውን - ዋጥ . . .ስልቅጥ ፤
ያነተረውን - ጭልጥ ፤
የጋጠውን - ቁርጥም ፤
ቁርጥምጥም ፤
ግጥም ፤
እንደ ውሃ ጥም ፤

ያረገዋል - እያመሰው ፤
ሞት ጉበዜ - ሞት ጆቢራው ።

በሰፈሩ -
ጭስ አይጨስም - በትዳሩ

ከዚያች ቀዬ - ከሞት አድማ ፤
ከዚያች መንደር - ከሞት ውድማ ፤
የእኒያ ነፍሳት - ጳጠሮ ፤
የሞት ሲሳይ - የባለ አጥቢያ ቀጠሮ ፤
ነፍሳት ፡- ረጭ ! እንዳሉ ዝም ፤
ሁሉም ፡- ዝም ! እንዳለ ዝም ፤

ምት ጉበዜ ፡- እያመስ ሲያፏጨው ፤
ያዘው ! . . . በለው ! . . . ሲል ምት ጆቢራው ፤

ዝምታቸው - የዝም ዝመው ፤ ላዩ - ላዩን - ተጨማምሮ ፡
ድምር ድምር - ተደማምሮ ፤
ዝም - ዝምታ አስገምግሞ . . . ኡኡታውን
“ስማሁ ” አለ ! - ዐይን ስማው !
ስማው ! ስማው ! . . .

“ ለንዳድ ጦስ - ማስታገሻ ፡- ለነስሉቱ ፤
ውሃ ! እያሉ ሲጠሩቱ ፤

ማንም ያምጣህ ፡ በግርም ምጣ ፤
ብቻ ውሃ . . .! ውሃ ሁነን የሚጠጣ . . . ”

አስገምግሞ ሲል - ዝምታው ፤
ማየት ሰማው ፤
ሰማሁ አለ . . . ሰማው ሰማው !

ያም ዝምታ ያስተጋባው . . . ከራራይስ
ከሰማያት ዘልቆ ደርሶ ፤

የመላክቱን ዝማሬ ምት . . . ሲያጣርሰው ፤
ሽብሻቦውን ፡- አንድነቱን . . . ሲያፋልሰው ፤
ሰማሁ - አለ ! . . . ማየት ሰማው
ሰማው - ሰማው ።

ወደ ላይም የሰማይ ጠል ከመላነቱ ፤
ከምድር በታች ጥልቅ ጉድጓድ ተሚጠጠ ቱርፋቱ
እልፍ ብሎ ግን . . .ወዲያ ማዶ ፤
እለ ነገር - ወዲያ ማዶ ።

መንደሯና ነገሩ . . . ወዲህና - ወዲያ ማዶ ፤
ሲተያዩ የኖሩ . . . በሩቅ እስሰር ተዛምዶ ።
እሷ - አትሔድ
እሱ - አይመጣ . . . ወይ ነዶ !
ሲያስገመግም - ያ ዝምታ
እየሰማ -
እንዳልሰማ . . . አካሔዱን የማይገታ ።

እወይ ወንዙ ! . . . ወንዙ ወንዛወንዙ !
ሽንጠ ጥምዝምዙ
አይ ወንዙ !
ይብላኝለት !
እን ማሙሽ ምን ይሉት !?

ለመርሳ መጠለያ

መስከረም 1978

አዋጅ ወላይ

ፍጥረት - ኑረት ፤
በሞት - ልውጠት ፤
በሌላ ምስል ዳግም ፍጥረት ፤
እና ኑረት ፤
አሐድ ድንግግ ነው ይሉናል - ኪነ - ሥርዓት ፤
ለሁሉ ዐይነት
በትክክል - ልክ ሥርጸት ፤

ይህም ሥርዓት ሲረጋገጥ ልክነቱ ፤
ውበት ገልቶ ፡-
ውበት ሲዋብ -

ውብ ጠንሰሰው . . . ክሒዶቱ ፤
አዋጅ . . . ! አሉን ፡- ለፈቀልን ያደላቸው ፤
እኒያ እማያውቁን - ሳናውቃቸው ፤
የዳሰሱን - ሳንቀርባቸው ፤

አሚን . . . ! እንደቃላቸው ፤
አሚን . . . ! እንደ ቃላቸው ።

30 - 3 - 82

ነ ገ

ነገ - ማለት : . . .

ቀርጠን . . . የማንሸርጠው ፣
በሳንዷቅ . . . የማንከተው ፣
የማርያም መቀነት - ዓይነት ነው ።

ስተ ያመና . . .

የኅብረ ቀለሟ ቅያሪ . . . በስሜት ቅርብ ሩቅነት . . . ሲባት፣
ምጥን ምስጢሯ ፦ . . . በመስጠር ሸራ ልባስ . . . ተሸሸጉ፣
ውብነቷን ፣
መዋብ እምሯን ፣
ፊዟን - ቁመን ፣

በመገረም ነሁልለን ስናይ ፣
ለመጋደድ እየከጀልን - ከየዓይነቷ ቅመሟ ፣
ጨልፈን ብልቃጥ ሳንያላት ፣
ትቅድመናለች መከሰሟ ።

በቃ . . . ነገ ማለት ፣
የዚህ - ዘር ናት ።

ለገርማ ታደሰ

4 - 8 - 82

የተከዳዳንለት

ከፊት ለፊቴ
አፍጦ . . . ፎቶ መስታወቴ ።
ከኋላዬም - ኋላ
አጥልቀብኝ - የሕሊና ጥላ

እፊት ኋላ እየዋለልሁ
ሁለት ምስሌን - እያለሁ . . . . . (በአንድነቴ)

ፊት ኋላዬን - እየተናኘሁ
እገመተምታለሁ . . .
" እኔ " ማለት - ይኽ ነኝ ?
" ይኽም " (እኔም)- እያደለሁኝ

ሁለቱን ሆኜ ይሆን - በአንድነቴ
ከፊት - ከኋላዬ ?

እኮ የቱንቱን ልመሰክር ?
የአንድ በላይ ስብጥርጥር
እያልሁ ።

9 - 1 - 82

ትቢያነትህ ይብቃ

ተነሥ . . . ንቃ ! - ቅጠል ታጠቅ ፣
አዳም ትቢያው ጭቃ ድቅድቅ ፤

አዳም ! . . . አዳም የምድር አፈሩ ፣
አዳም - የጭቃ ስፍሩ ፣

እፍ .ፍ.ፍ . . .እፍ.ፍ.ፍ.
ተነሥ አዳም ! ጭቃ ጥፍጥፍ ፣
እፍፍ - የሕይወት እስትንፋስ
አዳም ትቢያው ተነሥ !
ሒድ ! እስከ ወዲያኛው ፣
ሕያው ነፍስ ያለው ሰው ፣

ሆነህ - መጀመሪያ . . .
ለእንዲያ - እንዲያ -፣
በእንዲያ - እንዲያ - ፣

አዳም - ጭቃ !
ትቢያነትህ - ይብቃ ።

የከፈኑ - ዕዳ

. . ስፈር ነው እኮ ! ግራ ቀኙን . . . የየስማችሁን ኪሳራ ፣
ዕብቅ ጉድፉ በዛ’ይ . . . የረከሰ ስሜቱ አቧራ
የቅድስት ፍቅር ደንቃራ ፣
ያለመታደል ወረንጦ . . . ግልብ ግፊት ደንጎራ ፣
ከናንተ ኢያያዝ እንጂ . . . ፍቅር የላትም ሰባራ ።

. . . ምንም ይሁን - ምንም ብቻ ፣
አንደዬ ከቀረሳችሁ - ከፍቅር ሴማት እንጉቻ ፣
ፍቅር አዳራጇን እንጂ ራስን መሥራት ብትረሱ ፣
የሠራችሁትንስ - አታፍርሱ ።

ኤዲያ ተዉ !- ሰገንቷንስ አትናዱ ፣
በለምለሟ - እሪያ አትንዱ ።

ተዉ እንጂ እናንተ . . . ! አትሳቱ ፣
በምን ይታሻል - አሉአችሁ . . .ፍቅር ወለምታው ቅጭቱ።
የኮሲ ሙጃ ይመስላል . . . ያለ ወቅት አንገት መድፋቱ ፣
የእግር ጥፍርስ መመልከቱ ።

ይኸን ልብ - ይቅር ይበለው ፣
ውዴታን - እንቶ ለጠላው ፣-
ምንም ይብዛዛ - ቢሆን ፣
እያገባም ከቶ ለፍቅር - ማላበስ የመርገም ከፈን ።

ከማንኛችሁ ነው - ቅኝቱ ?
ፍቅር - ዜማዋ ብልሽቱ ፣
ቅዳሴዋንስ - የማዋቱ ።

እንዲያው - የከፈት እዳስ ለማነው ?
መዘዙ - የሚያተርፈው ።

ጥር 17 - 1977

የባሕር ማዶ ድምፅ

ውስጠ ባሕሬዬ - ሲሽምቅ ፣
ባሕሬ ሆዴ - ሲባባ ፣
ጨለማ ቀለም - ሲቀባ ፣
በዝምታዎቼ - ኮለል አምባ ፣
አይሰማችሁም - ነውጡ ! ?
ትርምርታዬ ፣
አይታያችሁም - ድጡ !?

አጨልቆ . . .

አወዳደቁን ለማፍጠን . . . ጀርባዬን ለመላላጡ ።
ቶሎ ይረግባል እንዴ . . . የደም ደጉ ?
እንዲህ አጭር ነው እንዴ . . . እትብተ ማጉ ?

ጥቁር አፈሯ . . . ጣዝማ ማሬ ፣
እንኮይ ሾላው . . . ያጋም ፍሬ ፣
ገደል ዱሩ . . . ግርማ ክብሬ ፣
ሜካ - ጢሻው ፡

የሩቅ - ፍቅሬ ፣
ያሁን - ፍቅሬ ፣
የ.ሩ.ቅ - ፍቅሬ ፣
ያ.ሁ.ን - ፍቅሬ ፣

የአገር ሰማይ - የአገር አድማስ ፣
የአገር ታቦት - ታቦተ - ንግሥ ፣
የአገር ሥራት - የአገር ዕድር ፣

የሩቅ . . . ፍቅሬ ፣
የሁን . . . ፍቅሬ ፣

ሲታዩ ነው - ወይስ አይታችሁ ?
ትዝታዬን - አለመጥራታችሁ ።
መታዘቢ ሳይለየኝ . . . እንዳለየው ፣
መታሰቢ - ገዝፎ ሳለ . . . እንዳልከላው ፣

እግሬ - ሲርቅ ፣
ልቤ - እንዳይርቅ ፣

የ.ሩ.ቅ . . .ፍቅሬ ፣
የ.ሁ.ን . . . ፍቅሬ ፣
ትዝታዬን - ትዝታዋን . . . ቶሎ ጥሩ ፣
ልል - እትብቴን . . . በጭር ቋጥሩ ።

24 - 10 - 80

ሕልም እውን ሲሆን

ሕልም ፡- እውን ሲሆን ያውቃሉ -?
እንግዲያውስ ልንገረዎት . . .ጆሮ ያለው ይስማ እንዲሉ ፣

. . . ከሚወዱት ወይም - ከልቦናዎ መክረው የወሰኑት ፣
ወዲያው በድርጊት - መንዝረውት ፣
የጉልበትዎን ዋጋ - የላብዎን ፍሬ ሲያገኙ ፣
በውጤትዎ ረክተው - ወናራም እንቅልፍ ሲተኙ ፣
ፍልቅልቅ ፡- ከሚል ሰላም ጋር ፣
ሐሳብ ፣ ትካዜ ፣ ጉስቁልና ተቀብሮ ፣

የሕይወት ዝብርቅርቅ ጠባሳ ፡
በድል ስሜት ሙላት ፦ ተውጦ ሲረሳ ፡
ሽንፍ ስብዕና ሲከስም ፡
በራስ መተማመን ፦ ዳግም እብቦ ሲለመልም ፡

የኔ ቅዠት መሳይ ሕልምም ቢሆን ፦

ይፈታል - ይሿል ፡

ለብኩን ምስኪን ሕይወት ፦

ጎህ ይቀዳል ፤

ብሩህ ወገግታ ይታያል ፤

ለሌላው ፤
ተስፋ ላመለጠችው ፤

ተስፋም ሆኖ ይገኛል ።

ለደረሰልኝ - ጥዱ ።

25 - 12 - 77

መተላለፍ

ያልተጻፈው ሕግ ፤
(ወግ) ፤
ከባለ አንቀጹ ይልቅ ጠብቆ ፤
ልቅልቅ- ፈቃዶችንን አድቆ ፤
ማኅበራዊነት - ተፈጥሮአዊነት ላይ ተጋድሞ ፤
ምንነት - ከማንነት ተጋጥሞ ፤

. . . የተዘገበበት ቀለሙ . . . .
የእመዳይ ጥርቅም ኩሬ ፤

ተረዳነው ንባብ :-

የ?አሻራችን ጥርጣሬ ።

ቆታይው :-
ቅጽበት የምትልሰው ፤
ጉሀ ሲያቃጣው በረኸርም ሙቀት ጨፈሩ
ቦና የሚበላው ነው ፤
እፍታው . . . የጤዛ ጨለቅሊቃ ባሕሩ ።
እንደ ተርቲብ ወሬ ዝንጠላ . . . መሸነጋገል ነው ክብሩ ፣
በሐራራ ዋንጫ ሲጨለጥ . . . የማይሰማ ማክሰሩ ።
ቀናትን ሲመነዝሩ ።

ብቻ :-
እንደ ተለያዩ ቀሩ ፤
ማንሜነት
እና 'ውነት ።

6-11-76

ምልዓት

በጥቂት የአምላክነት ባሕርዬ ፤
በትንሽ መመሳሰያ ፤
የአውሬ ሱስህን ክደህ ፤
ተሸጉጠህ እፍቅር ጉያ ፤
መውደድን እንደጠኔ ማርከሻ
በበጎ አድራጎት መርጨቱ ፤
ሕሊናህ " እምቢዮ!" ሲልህ
ነብሀ ታየብህ ምልክቱ ።
ሰው ነህና ።

25 - 11 - 82

ጉዞ

በሐሳብ ከሐሳብ . . . ጉድኝቱ ፣
ጅምር ከፍጻሜ . . . ቁርኝቱ ፣
እንዱ ሌላውን . . . በቅጥልጥሉ ፣
ሌላው ከሌላው ሲከታተሉ

. . . ሁሉ - የሁሉ ጅምር . . . በየረድፉ ፣
ሁሉ - የሁሉ እርጌ . . . በየዘርፉ ፣
ሁሉ - የሁሉ መነሻ
ሁሉ - የሁሉ መጨረሻ . . .

. . . እየተበቃቀ . . . ዙር በዙር ፣

እየተተካኩ . . . እግር በግር ፣

መቀጣጠል ነው . . . በሕይወት ቅጥልጥሊቱ ፣
በሐሳብ "ቢቃ" - እልባኑቱ ።
እዴ ! መቀጠል ፣
ለመቀጣጠል ።

22 - 4 - 82

ዝና አታብገር

. . . ያው ነው ! . . . በጅሽ ከሌለሁ ፣
ሞቻለሁ አሉ . . . እኔ ላንቺ ሞቻለሁ ፣
. . . ላንቺ ብቻ ሞቻለሁ ።

ይልቁን - ዝና አታብገር ፣
ጭራሽ - አትገብገር ።
የጅ ሥራ ነው . . . ሐውልት - ይናዳል ፣

እይጣሉ - ሲወርድ . . . ድንጋይ ይልማል ፣
አይጣል እንጂ ! . . . ከመጣ - አይጣሉ ፣
ዝግባ - ወይራ በስብሶ . . . ብረቶችም ይጐብጣሉ ፣
በሸብር ሽምቀ ተጋልበው . . . ፍጻሜአቸውን ያቀርባሉ ።

ስለዚህ

እዚያው - ከበቀልኩበት
ከተገጣጠምንበት ፣
ከዚያው ፡
ከውስጠ- ውስጠኛው

እንጂ . . .

ቀብሬን በከበረ ድንጋይ . . . ከብረት እንዳትሠሪ ፣
እዚያው . . . እዚያ ሥር . . . ሐውልቴን እልብሽ አኖቅሪ ።
መውደዴ ፡- ዝና እታብዤ ፣
ጭራሽ አትገበዤ ።

ለጣይዬ አቡዬ

14 - 5 - 82

ቀን - ዓመት

ዛሬ - በዋዜማው . . .

ለነገ ከርሞነት . . . እያማጠ ሳለ ፣

ትናንትን ለመሆን . . . እምናንም እከለ ።

ዛሬ በዋዜማው ።

ጳጉሜ 5 ቀን 1982

ቀብር

ሥርዓቱን እንዳች ሁለት

ሕሊናዬ ውጥረት አዘለ ፣

ይነዝረኛል - እናግለሁ ፣

አልወርድልህ ብሎኝ ቀለም ከብዕሬ ተንከባሎ ፣

ወደ ልቤ የሚፈሰው ፣

መሆን አለመሆን ግለቱ ፣

ይጨምቀኛል ፡-

የሕይወት ነጸብራቅ ግዝፈቱ . . .

. . .''ሕይወት እንዲህ ነው !''

ሲለኝ ከስተቱ ፣

''የሐቅ ሁነቱ ሐዲቱ ''

''እሺ . . . የውበት አምላክ

እሺ. . . የብዕር ጌታ '' እላለሁ ፣

ልነድፈው

ብዕር ከወረቀት እያዛመድሁ ።

ወዲያው ቃላት ተኾርኩደጉደው ፣
ብሂል ሆነው ፣ ብዕሬን አልፈው ፣
ጠብ ይሉ ብለህ ? . . . በምን ዕድሌ !
እንዲህ አይሆን ሁሌ ፣
እንዲህ አይሆን ሁሌ ።

ብዕሬን ካፎቱ ከተትኩኝ ፣
አማጥኩ ፣
በምጡ መሐል አሰብኩኝ . . .

ከማኖቹ ሊባተሰው ፣
የብን ግብር ሊቀይሰው ፣
ከዞሙን ዞመንቱ ሙብት ሊቅላ ፣
ባላ 'ያራም' - ነው ባለሰሌ ።

ቆይ . . . እስቲ . . .
ተራሮች . . . ይያሉቁ ፣
ሐይቆችም . . . ይናለቅሉቁ ፣
አራዊት . . . ይፈንደቁ ፣
ሰማያት . . . ጠል ያዝንቡ ፣
ዕጽዋት . . . ያወርቡ ፣

ምድር ባበቦች ትፍኳ . . . ይብሰል ያሸላ ፍሬ ፣
ሞገስ ከሽበት ይስማማ . . . ይደመቅ የሕዋናት ዝማሬ

የመቃብር አፉ ይከፈት ፣
ሞትም ይድረሰው - እንደ ሞት ።

የዚያን ጊዜ . . . ብዕሬ ቃል ያነባል ፣
ድብቅ ውበትን ይገልጣል ፣
እና . . . ምጤን እገላገላለሁ ፣
ብዬ . . . ቀጠሮ ይዣለሁ ፣
እልሃለሁ ።

መስከረም 1978

የቃላት መፍቻ

መሻት (4)

ጥልቅ ምኞት

ዛውያ (11)

የተከበረ ፣ የታፈረ ፣ የእስላም ቤተ - ጸሎት ፣

ዛት (20)

የሰው ውጫዊ ቁመና ፣ ሥጋ አካል
ዛቴን ሥጋአካሌን

ቴሽ (22)

እርግጫ (ካልቾ)

ጋቻ (26)

እጣን (እድሩስ) ማጨሻ ፣ ጊርጊራ

ዋሪ (34)

ቀትር

ሃይ, ሃያት (44)

ከሚዛን ወይም ከግምት በላይ የሆነ የትየለሌ የትና
የት

እርገረማው (45)

የአካልም የሕሊናም ድርብርብ ጉስቁልና

ቅሬ (45)

ዕድር ፣ ማኅበር

ኢፍታህ (46) ፍቱሕ - ይፈታ

የተማላ (58) የዋዛ ፡ የቀለድ፡

እንክርት (70) ተንቀሳቀሽ የእንጨት ማገዶ ማንደጃ

ዶሬ (71)

እልህ ፡ ወኔ

እሪየ (85)

ዓማማ

ተርቲብ (89)

የመንደር ቡና ጠጪዎች ማኅበር

የተለምዶ አገባብ ያላቸው ሐረጎችና ቃላት መፍቻ

ሙኖር አጅሬ (28)

"ሕይወት" የምንለውን ነገር በግርድፉ ሰውኛ ለማድረግና ከሰውም ለመነጋገር ስል የመረጥኩት ፤

ሞፎ (35)

ስለ ቁሳዊ ውነቶች እንጂ ስለ ውበት ወይም ኪነ ጥበብ ነገር ያንቋረነቱ የበገነው ጓደኛው (አናጋሪው) ሞፎ እንዲለው አረኩት ፤ በጥሬው ንሁልል ፤ ነፈዝ የምንለውን አይነት ሰውን

መጥፋት (45)

የኪነ ጥበብ ገላጭ የሆነው ጥበበኛ ፤ ውበትን ለመበርበር ሲል በሐሳቡ ተነጥሎ ሲነጉድ የሚታይበት የመመሰጥ ሁኔት . . . ይጥፉ ተዉት ከመመሰጡ ኢታነጥቡት ለማለት ነው ።

በግ ትልማት (45)

እሁነኛ ጸፊኝ . . የምትለው ስትመጣ ቀኑ የምታሳጣው . ስትዘንይ ተበላፈዋ የሚናፍቃት ፡ ስት ቀርብ የምናብ ና ስሉን የምታጎላለት . . . የሆነች ነገር ፣ የብዕር ጊታ ዛር ፣ ውቃቢም የሚሏት ፣

ሚሊዮ ማልበት (47)

ያልደመቀች ምናብ ፣ ደብዛዛ ራዕይ ፣ በቅዠትና በው መካከል ያለች እውነታና መሳለሚ ሆና ጠንሳይ ወይ ገላጭ በአጎር በርብሮ የሚጨብጣትን ለማለት .